# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 209 መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “ሀገርን ከጥቃት ማዳን የሚችል ጠንካራ የመከላከያ ኃይል ተገንብቷል”



- የቀድሞ ጦር ሰራዊት አመራር ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ሌሊሳ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ችግሮች ቢፈጠሩ እንኳን ሀገርን ከጠላት ጥቃት ማዳን የሚችል ጠንካራ የመከላከያ ኃይል ተገንብቷል ሲሉ የቀድሞ ጦር ሰራዊት አመራር ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ሌሊሳ ተናገሩ።

የቀድሞው የ18ኛ ተራራው ክፍለጦር አዛዥና የሶስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ምክትል አዛዥ የነበሩት ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ሌሊሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ጠንካራ የመከላከያ ሰራዊት መገንባት ተችሏል።

ቀደም ካሉ ዓመታት አንጻር በአደረጃጀቱ፣ በወታደራዊ ዝግጁነቱና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀሙ የዳበረ መከላከያ ሰራዊት መገንባቱ ታይቷል ያሉት ሜጀር ጀነራል መርዳሳ ፤ የሰራዊት ግንባታው በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አቅምን ማጠናከር ላይ ያተኮረ መሆኑን መታዘባቸውን አስረድተዋል።

በቅርብ ጊዜያት የምድር ጦሩንና የአየር ኃይል እንቅስቃሴዎችን በተለያዩ ማዕከላት ተገኝተው መነብኘታቸውን የተናገሩት የቀድሞው ጦር ሰራዊት አመራር፤

“ሀገርን ከጥቃት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## በአማራ ክልል ከ344 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ሳስመዘገቡ ባለሀብቶች ፍቃድ ተሰጥቷል

- ከወጪ ንግድ 96 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ሲገኝ ከ804 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማዳን ተችሏል
- 500 ሺህ ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም አላቸው

ገጽ 4






## መሳው ሕዝብና የክልል ልዩ ኃይል ከአሳሳች መረጃዎች በመራቅ የተማከለ ሠራዊት ለመገንባት ለተያዘው እቅድ እንዲተባበሩ ጥሪ ቀረበ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ የጥፋት አጀንዳ አራጋቢዎች ከሚሠራጩ አሳሳች መረጃዎች በመራቅ መላው ሕዝብ እንዲሁም የክልል ልዩ ኃይል አመራሮችና አባላት መንግስት ለጀመረው የየክልሉን ልዩ ኃይሎች ወደ ተለያዩ የጸጥታ መዋቅሮች እንዲገቡ ለጀመረው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስኬት እንዲረባረቡ መንግሥት ጥሪ አቀረበ፡፡

መሳው ሕዝብና... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

## በልማት ምክንያት ለተነሱ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ካሳና ምትክ መሬት ተሰጠ

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከተለያዩ ክፍለ ከተሞች በወንዝ ዳርቻና በልማት ምክንያት ለተነሱ 200 ነዋሪዎች እጣ በማውጣት የመኖሪያ ቤት አስረክበዋል። ለልማት ተነሺዎች የመሬት ካርታና 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ካሳም ተከፍሏል።

በርክክብ ሥነሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለፁት፤ የወንዞቻችን ዳርቻ አካባቢዎች በደረቅና ፍሳሽ እንዲሁም ከፋብሪካ በሚለቀቁ ቆሻሻዎች በመበከላቸው በዝናብ ወቅት በሰው ልጅ ጤና ላይ እንዲሁም በሰውና በንብረት ላይ አደጋ



በልማት ምክንያት ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል




# በኢትዮጵያ ያለው አክቲቪዝም ሚዛናዊነት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል


አቶ ፈቃዱ ዓለሙ


ወይዘሪት ዮርዳኖስ ግዛቸው

**አመለወርቅ ከበደ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በኢትዮጵያ ያለው የማህበራዊ ሚዲያ አክቲቪዝም ሚዛናዊነት ላይ ያተኮረና ተጨባጭ መረጃዎች ላይ የተመረኮዘ ሊሆን ይገባል ሲሉ የዘርፉ ባለሙያዎች ተናገሩ፡፡

የኢትዮጵያ ናሽናል ሚዲያ ሳፖርት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈቃዱ ዓለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ያለው አክቲቪዝም ሚዛናዊነት ላይ ከማተኮርና ለትክክለኛው አላማ ከመቆም ይልቅ የአንድን ወገን ጥቅም ለማስከበር የቆመ ነው፡፡

አቶ ፈቃዱ እንደተናገሩት፤ አክቲቪዝም በሰዎች የኑሮ ስርዓት ውስጥ መሻሻል የሚገባቸውን ጉዳዮች የማመላከት፣ ችግሮችን በምክንያታዊነት ነቅሶ የማውጣትና መፍትሄ የማፈላለግ እንዲሁም የህዝቦችን ነጻነት የሚጋፉ ጉዳዮች ሲኖሩ ለዜጎች ጥብቅና የመቆምን አላማ ያነገበና በነፃነት የመናገር የሰብዓዊ መብት የሚተገበርበት ሂደት ነው።

በዓለም ላይ በሰብዓዊ መብቶች ፣በፍትህ ፣ በሚዲያ ነፃነት፣ በሴቶች እኩልነት ላይ አግባብ ያልሆኑ ጥሰቶች ሲፈጸሙ እና መቀየር ያለባቸው ህጎች ፣ባህሎች ሲመጡ ለበጎ ለውጥ የተነሳሱ አክቲቪስቶች ድምጻቸውን ያሰማሉ ብለዋል።

ነገር ግን በኢትዮጵያ የሚታየው በአብዛኛው ከዚህ ያፈነገጠ ነው ያሉት አቶ ፈቃዱ፤ በአብዛኛው ጽንፍ የመያዝና ግጭትን የማባባስ አዝማሚያ ይታይበታል ሲሉ አስረድተዋል።

በሀገራችን ለውጦች እንዲመጡ፣ የስርዓት መሻሻል እንዲፈጠር እና ፍትህ እንዲሰፍን የታገሉ አክቲቪስቶች እንዳሉ ሁሉ ሙሉ ጊዜያቸውን በግጭት ማባባስና አንድነታችንን በሚፈታተኑ ጉዳዮች ላይ የሚያውሉ አክቲቪስቶችም አሉ ብለዋል።

አቶ ፍቃዱ እንዳስታወቁት፤ አሁን ላይ በኢትዮጵያ ያለው አክቲቪዝም ከትክክለኛው አላማ ይልቅ የአንዱን ብሄር፣ ቡድን በተለየ መልኩ ተጠቃሚ ለማድረግና ያልተፈለገውን አካል በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲጠላ ለማድረግ ይውላል። አለፍ ሲልም ወንጀልን ለመሸፋፈን የተዛባ መረጃ የሚለቁ ጭምር የሚገኙበት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

የአገርንና የህዝብን ሁለንተናዊ ዕድገት ለመደገፍ አክቲቪስቶች ሃቀኛና፣ በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመረኮዙ መረጃዎችን በማውጣት፤ ህዝብን ከጥፋትና አገርን ከጉዳት መከላከል ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ገልጸዋል።

በተጨማሪ ውጤታማ አክቲቪዝም እንዲኖር የትኛው አክቲቪስት ለትክክለኛው አላማ የቆመ ነው? ምን ያክል ተዓማኒ መረጃ ያወጣል? የሚሉ ጉዳዮች ላይ ጥናት መደረግ አለበት ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ትምህርት ክፍል ኃላፊ ወይዘሪት ዮርዳኖስ ግዛቸው በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ ከታዩ የአክቲቪዝም ጽንፈኛ እንቅስቃሴዎች አንጻር ቀደም ካለው ጊዜ አሁን ላይ የተወሰነ መሻሻል ቢታይም ሊታረቁ የሚገባቸው ጽሁፎችን በማህበራዊ ሚዲያው የሚለቁ አክቲቪስቶች አሉ።

አንዳንድ አክቲቪስቶች አንዱን ቡድን ለመጥቀም፣ ሌላኛውን ለመጉዳት አልያም የእኔ ለሚሉት ወገን ብቻ ጥብቅና በመቆም ሲከራከሩ ይስተዋላል፤ ይሁንና ይህ አካሄዳቸው ስህተት መሆኑን በመገንዘብ ለሁሉም ህዝብ ፍትህ፣ ነጻነትና እኩልነት እኩል ድምጽ ሊያሰሙ ይገባል ብለዋል።

በዓለም ተሞክሮም ብዙ አገራት አክቲቪስቶችን ተጠቅመው የተለያዩ ለውጦችን አምጥተዋል ያሉት ወይዘሪት ዮርዳኖስ፤ እንደ አብነትም የባርነት ንግድ ስርዓትን ለማስቀረት፣ አምባገነናዊ ስርአትን ለመጣል እና በምክንያታዊነት ላይ የተመረኮዙ የፖለቲካ ምርጫዎችን ለማሸነፍ በበጎ ጎን እንደተጠቀሙበት አስረድተዋል።

በኢትዮጵያም ውጤታማ አክቲቪዝም እንዲኖር በሚዛናዊነት ሁሉን ባህል፣ ቋንቋ እና ሃይማኖት አሳታፊ ቢያደርጉ ማህበረሰቡን የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋሉ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# በሀረሪ ክልል በ200 ሚሊዮን ብር የትምህርት ቤት ግንባታና እድሳት ተከናወነ

**ጌትነት ምህረቴ**

<u>ሀረር</u>፡- በሀረሪ ክልል በ200 ሚሊዮን ብር ግንባታቸው ሲካሄድ ከቆዩ ስምንት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስድስቱ ግናባታቸው ተጠናቆ ስራ መጀመራቸውን የክልሉ ትምህርት ቢሮ ገለጸ።

የሀረሪ ክልል ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ ዐቢይ አበበ እንደተናገሩት፤ በክልሉ የትምህርት ተደራሽነትን ለማረጋገጥና ጥራትን ለማስጠበቅ 200 ሚሊዮን ብር ያህል ወጪ በመመደብ የስምንት ትምህርት ቤቶች ግንባታ ተካሂዷል። ግንባታቸው ሲካሄድ ከቆዩ ስምንት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስድስቱ ተጠናቀው ዘንድሮ ስራ ጀመረዋል። ቀሪዎቹ ሁለቱ በቅርቡ ተጠናቀው የሚመረቁ ይሆናል።

በክልሉ ከተገነቡት ስምንት ትምህርት ቤቶች አራቱ በገጠር ቀበሌዎች የሚገኙ መሆናቸውን አመልክተው፤ አራቱ ደግሞ በከተማ የተገነቡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የተገነቡት ትምህርት ቤቶች ቀድመው በዕርጅና ምክንያት እየፈራረሱ የነበሩ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ እነዚህን ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ አፍርሶ የመገንባት የማደስ፣ የማስፋፋት እና አዲስ ግንባታንም የሚጨምሩ መሆናቸውን አብራርተዋል።


ፎቶ፡ሃዱሽ አብርሃ

የሉዑል ራስ መኮንን ትምህርት ቤት ዕድሳትና የማስፋፊያ ግንባታም በቅርቡ ተጠናቆ እንደሚመረቅ በአብነት ጠቅሰዋል ።

ትምህርት ቤቶቹ ተጠናቀው ስራ በመጀመራቸው ተማሪዎች ሳይጨናነቁ ጸዱና ለዕይታ በሚስቡ ትምህርት ቤት እንዲማሩና ውጤታማ እንዲሆኑ የሚረዳ መሆኑን ነው የተናገሩት።

በሀረር ከተማ የሚገኝ 150 ተማሪዎች ይማሩበት የነበረ አንድ ትምህርት ቤት ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ፈርሶ በአዲስ መገንባት በመቻሉ በአሁኑ ጊዜ 600 የሚደርሱ ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረ እንደሚገኝ በምሳሌነት አስረድተዋል።

በአሁኑ ጊዜም በክልሉ ቁጥራቸው ውስን የሆነውን ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ለማስፋፋት አምስት ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ግንባታ እየተካሄደ እንደሚገኝም አመልክተዋል ።

በክልላችን አሁን ላይ ተማሪዎች ከአምስት ኪሎ ሜትር በላይ ተጉዘው የሚማሩበት ቀበሌ የለም ያሉት አቶ ዐቢይ፤ በአገርም ሆነ በክልላችን ያለውን የትምህርት ጥራት ችግር ለመፍታት የትምህርት ቤቶቹ ግንባታ ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረውም ነው ያብራሩት። በክልሉ በትምህርት ተደራሽነት ላይ ብዙ ችግር ባይኖርም ጥራት ላይ ግን ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠይቃል ብለዋል።

# የፊቼ-ጨምበላላ በዓልን በደመቀ መልኩ ለማክበር ዝግጅት እየተደረገ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የሲዳማ ክልል የዘንድሮውን የዘመን መለወጫ (የፊቼ-ጨምበላላ) በዓልን በደመቀ መልኩ ለማክበር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የሲዳማ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ አበበ ማሪሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሚያዝያ 11 እና 12 ቀን 2015 ዓ.ም በደማቅ ሁኔታ የሚከበረውን የፊቼ-ጨምበላላ በዓልን በተሳካ ሁኔታ ለማክበር በየሴክተሩ የተለያዩ የዝግጅት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜም ቢሮው ሆቴሎችን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ የትራንስፖርት ዘርፍን፣ አስጎብኚ ድርጅቶችና ሌሎች የእንግዳ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በማካተት እንግዶችን ለመቀበል የዝግጅት ስራዎችን እያከናወነ ነው፡፡



የፍቼ ጨምበላላ በአል የአለም ቅርስ እንደመሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ ከ16 በላይ ሆቴሎች ለአገር ውስጥና ለአለም አቀፍ ጎብኚዎች እንግዶቻቸውን ለመቀበል ከወዲሁ መዘጋጀታቸውንም ተናግረዋል።

አቶ አበበ በአሉ በዩኔስኮ በማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ከተመዘገበ ወዲህም የበርካታ ሰዎችን ቀልብ እየሳበ ከሀገር ውስጥም ከውጭም የሚሳተፉ ጎብኚዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን አመልክተዋል፡፡

ምክትል ኃላፊው እንዳስታወቁት፤ በዘንድሮው የፍቼ -ጨምበላላ በዓል ላይ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ጎብኚዎች ይሳተፉበታል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሆቴሎችን፣ትራንስፖርትና ሌሎች ዘርፎችን ተጠቃሚ ስለሚያደርግ ኢኮኖሚውን የሚያነቃቃ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የዘንድሮው የፊቼ ጨምበላላ በአል በክልሉ ዋና ከተማ ሀዋሳ ላይ ለሁለት ቀናት ለማክበር የታቀደ መሆኑን ጠቁመው፤ ሚያዝያ 11 ቀን 2015ዓ.ም በሲዳማ ባህል አዳራሽ ላይ የተለያዩ ዝግጅቶችና የክብር እንግዶች በተገኙበት ይከበራል፡፡ ሚያዚያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ላይም ሀዋሳ ሀይቅ አጠገብ ባለው ትልቁ ጉዱማሌ ላይ በተለያዩ ባህላዊ ዝግጅቶች የሚከበርና በስነ ስርዓቱ ላይም በርካታ ጎብኚዎች እንደሚታደሙበት ይጠበቃል ነው ያሉት፡፡

የፊቼ ጨምበላላ በአል የሲዳማ ብሄረሰብ ዘመናዊ አኗኗርና በተለይም ጊዜን መለካት ከጀመረበት ጊዜ ጋር ይቆራኛል ያሉት ኃላፊው፤ ይህም በጨረቃ ላይ የተመሰረተ የጊዜ ቆጠራ ቀመር የሚከተል እንደሆነና እንደ ጥንታዊ ስልጣኔ የሚቆጠር መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

ኮከብ ቆጣሪዎች በየዓመቱ የበዓሉን ትክክለኛ ቀን ወስነው ከዚያም ለጎሳዎቹ እንዲነገር የሚደረግ ሲሆን እድሜ፣ ጾታ እና ማህበራዊ ሁኔታ ሳይለይ በይቅር ባይነት ፣በፍቅርና በአብሮነት የሚከበር ትልቅ እሴት ያለው በአል መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ አበበ ገለጻ፤ ፊቼ ጨምበላላ የሲዳማ ህዝብ ካልተገቡ ድርጊቶች ሁሉ ታቅቦ የሚያከብረው በአል ሲሆን፤ እንደ እንስሳት ማደን፣ ዛፎችን መቁረጥ ከመሳሰሉ ድርጊቶችም ጭምር የሚታቀብበት ወቅት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡


ወይዘሮ አበንግ ኩመዳን

# ለዓባይ ግድብ 500 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማሰባሰብ ንቅናቄ ሊጀመር ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ለዓባይ ግድብ ከነገ ጀምሮ በሚካሄድ ሀገር አቀፍ ንቅናቄ 500 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ እንደሚንቀሳቀስ አስታወቀ፡፡

የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ምክትል ፕሬዚዳንትና የሊጉ የጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ አበንግ ኩመዳን በትናንትናው ዕለት በሰጠችው ጋዜጣዊ መግለጫ፤ የሀገሪቱ ትልቅ ሀብት የሆነውን ዓባይ ግድብ ከግብ ለማድረስ ሊጉ የገቢ ማሰባሰብ ንቅናቄ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል በማካሄድ ከቦንድ ግዢ 500 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡

‹‹ወጣት ለህዳሴው እኔም ድርሻ አለኝ›› በሚል መሪ ሀሳብ የሚካሄደው የገቢ ማሰባሰቢያ መርሃ ግብር ከሊጉ አባላት እና ከየማኅበረሰቡ የቦንድ ግዢ ለማሰባሰብ እንደሚሠራ ወጣት አበንግ ገልፃለች፡፡

በብልፅግና ወጣቶች ሊግ ሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን አባል የሆኑ ወጣቶች መኖራቸውን የጠቀሰችው ኃላፊዋ፤ ከዚህ ውስጥ ግማሹን በመጠቀም ገቢ ለማሰባሰብ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሳለች፡፡

ባለፉት አስራ ሁለት ዓመታት ወጣቱ ለህዳሴው ግድብ ገንዘቡን፣ ሀብቱንና እውቀቱን በመስጠት የበኩሉን ድርሻ ሲወጣ ቆይቷል ያለችው ወይዘሮ አበንግ፤ ግንባታው 90 በመቶ የደረሰውን ግድብ ለማጠናቀቅ በሚደረገው ተሳትፎ ወጣቱ ጉልበትና አቅሙን አሟጦ እንዲጠቀምና ታሪክ እንዲሰራ ጥሪ አቅርባለች፡፡ የቦንድ ግዥ ንቅናቄው በድሬዳዋ ከተማ በነገው ዕለት እንደሚጀመርም ምክትል ፕሬዚዳንቷ አሳውቃለች፡፡ በንቅናቄውም በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ወጣቶች ተሳትፎ በማድረግ አሻራቸውን እንዲያስቀምጡ ጥሪ አቅርባለች፡፡

የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ በሀይሉ አብረሃም በበኩላቸው፤ ንቅናቄው በመላው ሀገሪቱ በተለያዩ መርሀ ግብሮች የሚከናወን ሲሆን፤ በተከታታይ ዙሮች የውሀ ሙሌት ተከናውኖለት ወደ ሀይል ማመንጨት የተሸጋገረው ግድብ እስከ ፍፃሜው እንዲዘልቅ ወጣቶች ታላቅ አቅም እንደሆኑ የሚያሳይ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ወጣቶች በተናጠልም ሆነ በቡድን ቦንድ በመግዛት ወደ ብልፅግና ለሚደረገው ጉዞ ትልቅ አቅም የሆነው ግድብ እንዲጠናቀቅ ብሎም በኢትዮጵያ ብልፅግና ላይ ትውልዳዊ አሻራቸውን ማኖር እንዲችሉ ይህ ትልቅ እድል መሆኑን ተረድተው በንቅናቄው ላይ በትጋት እንዲሳተፉ ጥሪ ያቀረቡት አቶ በሀይሉ፤ በሊጉ የተጀመረው እንቅስቃሴ እጅግ ይበል የሚያሰኝ ተግባር በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወጣት ያለምንም ልዩነት በንቅናቄው ላይ መሳተፍ እንደሚገባው ተናግረዋል።

# ሃይማኖታዊ በዓላቱ ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲከበሩ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ሳምንታት የሚከበሩት የትንሳዔና የኢድ አልፈጥር በዓላት ያለምን የፀጥታ ችግር እንዲከናወኑ ከወዲሁ የቅድመ ዝግጅት ስራ እየተሰራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ የሰላምና የፀጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ጌታሁን አበራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በቀጣይ የሚከበሩትን የትንሳዔና የኢድ አልፈጥር በዓላት ያለምንም የፀጥታ ስጋት ማህበረሰቡ በሰላም እንዲያከብር ከወዲሁ የቅድመ ዝግጅት ስራ እየተሰራ ነው፡፡

ስርቆት፣ ነጠቃ፣ ሀሰተኛ የብር ኖትና የተጭበረበረ ሰነድ ማሰራጨት የመሳሰሉት ወንጀሎች በብዛት በበዓላት ጊዜ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ናቸው ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ እነዚህን ወንጀሎች በመከላከል የትንሳዔና የኢድ አልፈጥር በዓላት ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲከበሩ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

በመዲናዋ የሚኖሩት የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች አምልኮታቸውን በየቤተ እምነታቸው በሰላም አክብረው እንዲመለሱና በዓሉን ያለምን የፀጥታ ችግር እንዲያከብሩ ተቋሙ ከባለድርሻ


**አቶ ጌታሁን አበራ**

አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ መሆኑን አቶ ጌታሁን ተናግረዋል፡፡

የሚከበሩትን በዓላት መነሻ በማድረግ በገበያ ስፍራዎችና በሌሎች አካባቢዎች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመቆጣጠርና ለመከላከል ለፀጥታ ኃይሉ ስምሪት የመስጠትና ማህበረሰቡን የማወያየት እንዲሁም የማሰልጠን ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ጌታሁን አክለውም፤ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ ከማድረግ ባለፈ የከተማዋን ሰላም፣ ደህንነትና ፀጥታ በማስከበርና የፀጥታ ስጋቶችን በዘላቂነት ለመቅፍ በትኩረት እየተሰራበት ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በትንሳዔና በኢድ አልፈጥር በዓሎች ወቅትም ለሰላም ስጋት የሆኑ ቦታዎችን በጥናት የመለየት ስራ መሰራቱን ጠቁመው፤ የፀጥታ ስጋት አለባቸው ተብለው በተለዩ ቦታዎች በቂ የሆነ የፀጥታ ኃይል ስምሪት ይደረጋል ብለዋል፡፡

የመዲናዋ ማህበረሰብ የትንሳዔና የረመዳን በዓላት በሰላም እንዲከበሩ የሃይማኖት አባቶችን ያሳተፈ ስራ ይሰራል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

በበዓላት ወቅት በአቋራጭ ለመክበር በምርታቸው ላይ ባዕድ ነገር ጨምረው ከሚሸጡ ስግብግብ ነጋዴዎች ማህበረሰቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባውና በምግብ ነክ ነገሮች ላይ ባዕድ ነገሮችን ጨምረው የሚሸጡ ነጋዴዎች ሲያጋጥሙት ለፀጥታ አካላት ጥቆማና መረጃ በመስጠት ወንጀልን በመከላከል ረገድ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል ብለዋል፡፡



# በቦረና የ10 ግድቦች ግንባታ በቀጣዮቹ ሁለት ወራት ይጠናቀቃል

**አስቴር ኤልያስ**

ያቤሎ፡- በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን እየተሰሩ ካሉ 14 የግድብ ፕሮጀክቶች ውስጥ አስሩ በቀጣይ ሁለት ወር እንደሚጠናቀቁ የኦሮሚያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ምክትል ኃላፊ እና የመስኖና ኢነርጂ ዲቪዥን ሄድ ኢንጂነር ዳዊት በቀለ አስታወቁ፡፡

ኢንጂነር ዳዊት ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፤ በቦረና ዞን 14 የግድብ ፕሮጀክቶች ተጀምረው ወደስራ ገብተዋል፡፡ እነዚህ ግድቦች ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የተገነቡ ሲሆን፤ ከ14ቱ ውስጥ አስር ያህሉ በመጪዎቹ ሁለት ወራት፤ ቀሪዎቹ አራቱ ደግሞ በቀጣይ መስከረም ወር ይጠናቀቃሉ፡፡

ኢንጂነር ዳዊት እንደተናገሩት፤ በኦሮሚያ ፊና ኦሮሚያ የሚል ፕሮግራም የተጀመረ ሲሆን፣ በክልሉ ዝናብ አጠር ዞኖች ላይ ለአራት ዓመት የሚቀጥል ሆኖ ወደስራ የገባ ነው፡፡ በዚህ ፕሮግራም ስራ ላይ እንደክልል ያሉት 73 ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ በፕሮጀክቱ የተመረጡ አካባቢዎች በድርቅ የሚጠቁ ሲሆኑ፣ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ቦረና ዞን ነው፡፡

የፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ዓላማ ዝናብ መያዝ ነው ያሉት ኢንጂነር ዳዊት፤ ውሃ ካለ ሕይወት አለ እንደማለት ነውና ግድቡ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያለው ነው ብለዋል፡፡ ግድቦቹ ለሰውና ለእንስሳት መጠጥነት የሚያገለግሉ እንደሆኑ ጠቅሰው፤ በቀጣይ ደግሞ ለመስኖና ለዓሳ ርባታ ጭምር አገልግሎት ላይ የሚውል ነው ብለዋል፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፤ በቦረና ዞን አሁን የተያዘው ውሃ የአንድ ሳምንት ውሃ ነው፤ ውሃው ከተያዘ ለሚቀጥለው ስድስትና ሰባት ወር ያህል ያለ ስጋት መጠቀም ያስችላል፡፡ ዝናቡ በዞኑ ሁለቴ የሚዘንብ ስለሆነ ይህ መያዙ ብቻ ትልቅ እፎይታን የሚፈጥር ነው፡፡

እንደ ኦሮሚያ ክልል በዝናብ አጠር ዞኖች 73 የግድብ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ መሆናቸውን ገልጸው፤ በዚህም ወደ 700 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ መያዝ ይቻላል ብለዋል፡፡ ይህ ውሃ ደግሞ 50 ሺ ሔክታር መሬት ማልማት እንደሚያስችል ተናግረው፤ ይህም ከመቶ ሺ በላይ አባወራን ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ትልልቅ ግድብ ተብሎ አስር እና ከዛ በላይ ዓመት የሚወስድ ሲሆን፤ ይህ ግን በ18 ወር ይጠናቀቃል ተብሎ ከወዲሁ በስምንት ወር ሊጠናቀቅ ችሏል፡፡

በኦሮሚያ ኢንጂነሪግ ኮርፖሬሽን የያቤሎ ክላስተር አስተባባሪ ኢንጂነር ምትኩ ተሾመ በበኩላቸው እንዳሉት፤ የፉናን በሬሳ ግድብ ከፍታው 21 ሜትር ሲሆን፣ የሚይዘው 17 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ በቅርቡ በዘነበው ዝናብ 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ መያዝ ተችሏል፡፡ ግድቡ ከተጀመረ ስምንተኛ ወሩን የያዘ ሲሆን፣ ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደው ግን በ18 ወራት ውስጥ ነው፡፡ ይሁንና በአስር ወር ውስጥ ይጠናቃል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በጋዜጠኞች ከተጎበኙት ግድቦች ውስጥ አንዱ ፊና ዎርባቴ ግድብ ፕሮጀክት ሲሆን፤ ይህ ግድብ 96 በመቶ መጠናቀቁን የፊና ዎርባቴ ግድብ ፕሮጀክት አስተባባሪ ኢንጂነር ዋቅጅራ ቢረሳ ተናግረዋል፡፡ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ 120 ሔክታር መሬት ማልማት ይችላል ሲሉ ጠቅሰው፤ በአሁኑ ሰዓት የያዘው ውሃ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሜትር ኪዩብ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ውሃው የተያዘውም በሁለት ቀን ዝናብ እንደሆነም አመልክተዋል፡፡

ዜና

# በአማራ ክልል ከ344 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች ፍቃድ ተሰጥቷል

- ከወጪ ንግድ 96 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ሲገኝ ከ804 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማዳን ተችሏል
- 500 ሺህ ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም አላቸው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በተፈጠረው ሰላም ባለፉት ሰባት ወራት 344 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሃብቶች ፍቃድ መውሰዳቸውን የክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ገለጸ፡፡ በክልሉ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ከ96 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ሲገኝ ከ804 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማዳን ተችሏል ብሏል፤ ኢንዱስትሪዎቹም 500 ሺህ ለሚደርሱ ዜጎች የስራ እድል የመፍጠር አቅም እንዳላቸው ተጠቁሟል፡፡

የአማራ ክልል ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ እንድሪስ አብዱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት የነበረው ግጭት የክልሉን ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ሁኔታ ጎድቶት የነበረ ቢሆንም በየሰላም ስምምነቱ ምክንያት ካለፉት ሁለት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር በዘንድሮ በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴው በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡

በዚህም ባለፉት ሰባት ወራት 344 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ኢንቨስትመንቶች ፍቃድ ወስደዋል፡፡

እንደ አቶ እንድሪስ ገለጻ፤ ኢንቨስትመንቱ ከፍተኛ መሻሻል ያሳየዉ በኢንቨስትመንት ቁጥር ብቻ ሳይሆን በካፒታል መጠን



አቶ እንድሪስ አብዱ

እንዲሁም አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በሚጠይቁ በውጭ እና በአገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ስብጥር ጭምር ነው፡፡

አማራ ክልል አሁን ባለው ሰላም እና መረጋጋት ለኢንቨስትመንት ተመራጭ እየሆነ መምጣቱን ተናግረው፤ የሚመጣው ኢንቨስተር በብዛት፣ በካፒታል መጠን እና በስብጥርም የተሻለ እንደሆነ ቢሮው መገምገሙን ገልጸዋል፡፡

ባለፉት ሰባት ወራት 344 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ከሁለት ሺህ 575 የሚበልጡ አዲስ ኢንቨስትመንቶች ፍቃድ ማግኘታቸውን ጠቁመው፤ አዲስ የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰጣቸው ኢንቨስትመንቶች በቂ ክትትል እና ድጋፍ ተደርጎላቸው በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ ሲገቡ 500 ሺህ ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ ገልጸዋል፡፡

በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተጀመረው "የኢትዮጵያ ታምርት" ንቅናቄ በክልሉ ራሱን የቻለ የኢንቨስትመንት አሻራ ማሳረፉን የገለጹት አቶ እንድሪስ፤ በተያዘው በጀት ዓመት ብቻ 34 አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ በመላክ 96 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዳገኙ ተናግረዋል፡፡

መንግስት ከዚህ ቀደም ከፍተኛ ወጪ እያወጣ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ተኪ ምርቶች በማምረትም በክልሉ 98 ኢንደስትሪዎች መንግስት ያወጣ የነበረውን ከ804 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ማዳን መቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

የክልሉ መንግስት አምራች ኢንዱስትሪዎችን በሚመለከት መሬት በምደባ የሚተላለፍበት ልዩ መመሪያ ባዘጋጀው መሰረት ለ288 ኢንዱስትሪዎች 414 ነጥብ ዘጠኝ ሄክታር መሬት እንዲሁም ከ153 በላይ ለሆኑ ለግብርና እና ሌሎች ዘርፎች 19 ሺህ 694 ሄክታር መሬት በምደባ ማስተላለፉን አክለው ገልጸዋል፡፡

ክልሉ ለባለሀብቱ ምቹ የተረጋጋ የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታን መፍጠር ላይ በሚገባ እየሰራ እንደሆነ የሚገልጹት አቶ እንድሪስ፤ አልፎ አልፎ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማረም በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ስር የኢንቨስትመንት እና የኢንዱስትሪ ጉዳዮችን የሚመለከት የሥራ ክፍል በማደራጀት ክልሉ የግል ባለሀብቱ ሀብት እና ንብረት እንዲጠበቅ ሙሉ ኃላፊነት ወስዶ እየሰራ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶችን የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ ችግሩን ለመፍታት የኤክስፖርት አቅምን ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመ፤ ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ የሚልኩ ኢንዱስትሪዎችን አቅም በማሳደግ የምንዛሪ ችግርን በመፍታት የግብዓት አቅርቦት ችግርን በዘላቂነት መፍታት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

የኢንቨስትመንት ሥራ የብዙ ተቋማትን እና ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ ከተቋማት ጋር ያለው ቅንጅት ከተሻሻለ፤ የኃይል አቅርቦት ችግርን በዘላቂነት መፍታት ከተቻለ እና ሁሉም የየራሱን ድርሻ ከተወጣ በሚቀጥሉት ጊዜያት በክልሉ የተሻለ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እንደሚኖር ተናግረዋል፡፡

## “ሀገርን ከጥቃት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በጉብኝታቸው ወቅት የሰራዊቱ አንድነትና ቅንጅታዊ ስራ ሀገራዊ ግዳጆችን በተሻለ አፈጻጸም ለመከወን የሚረዳ መሆኑን መገንዘባቸውን ተናግረዋል።

ሜጀር ጀነራል መርዳሳ እንደገለጹት፤ በአፋር አዋሽ 40 እና በመስቀል አደባባይ የታዩ ወታደራዊ ትርዒቶችም መከላከያ ሰራዊት ምን ያክል በዘመናዊ ትጥቆች እየተጠናከረ መምጣቱን በግልጽ አሳይተዋል።

የአየር ኃይሉና የምድር ጦሩ በየዘርፋቸው እራሳቸውን ለማጠናከር የሚወስዷቸው ርምጃዎች ሰራዊቱ ሀገር የማዳን ግዳጅ ቢመጣበት በብቃትና በፍጥነት ኃላፊነቱን መወጣት እንደሚችል ያረጋገጡ ናቸው ሲሉ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ከመደበኛ ወታደር በተጨማሪ የኮማንዶና ልዩ ግዳጅ ስልጠና አቅምን ማጠናከር መቻሉን መታዘባቸውን ተናግረው፤ መከላከያው በምድርና በአየር ኃይል አቅም እንዲደረጅ እንዲሁም በባህር ኃይል ዳግም ምስረታው እንዲጠናከር የሚረዱ ስራዎች መጎልበት አለባቸው ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የሀገር ሉዓላዊነትን በማስከበር ሂደት ውስጥ ውትድርና ከፍተኛ ትጋት የሚጠይቅ ሙያ ነው፤ በዚህ ረገድ የሰራዊቱን አቅም የሚያሳድጉ ዘርፈ ብዙ የአቅም ግንባታና ስልጠና ስራዎች ቀጣይነት ሊኖራቸው ይገባል ብለዋል።

ሜጀር ጀነራል መርዳሳ እንደገለጹት፤መላው ሕዝብ ኢትዮጵያ ወደ ዘላቂ ሰላሟና አንድነቷ እንዳትመለስ የሠራዊቱ ሚና ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ለሰራዊቱ የሚሰጠውን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ኢትዮጵያ ካላት ሰፊ የመሬት ይዞታ አኳያ መከላከያ ሰራዊቱ መላው አካባቢ ላይ ሰፍሮ ሀገሩን መጠበቅ ስለማይችልም፤ ሰራዊቱ ወሳኝ በሚባሉ ቦታዎች ላይ መቀመጥ እንዳለበት አቅጣጫ መያዙም ተገቢ ነው ብለዋል።

ከዚህ አንፃር በየአካባቢው ያለው ሕዝብም ሰላም የሚያውኩ ጉዳዮችን በመከላከል የሰራዊቱን ጫና መቀነስ እንዳለበት ጠቁመዋል።

በተለይ ወረዳዎች የፖሊስ ፀጥታ አካላት አቅማቸውን በማጎልበት አነስተኛ ችግሮች ሲፈጠሩ በእራሳቸው አቅም መከላከል የሚችሉበትን መንገድ ማጠናከር አለባቸው። እያንዳንዱ ዜጋ ከጸጥታ አካሎች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ከሆነ ሀገራችን ዘላቂ ሰላሟን ታገኛለች ሲሉ ገልጸዋል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕብረ ብሔራዊነትን የተላበሰ ወጥ የጸጥታ እና የመከላከያ ኃይል መፍጠር ወሳኝ ነው

የአንድ ሀገር ህልውና የሚጸናው በሕዝቦቿ የሀገር ፍቅር ጽናትና በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ተቋማት ጥንካሬ እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም ሲባል ሀገራት በሀገር ፍቅርና በተቋማት ግንባታ ዙሪያ ሁሌም ያለመታከት ይሰራሉ፤ በድካማቸውም ፍሬ ጠንካራ ሀገር እና ሕዝብ በመመስረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸውን ተሰሚነትና ተጠቃሚነት ያጎለብታሉ።

በዚህ ረገድ ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት መሰረት የሆነውን ውጪያዊና ውስጣዊ ሰላም እና ሀገራዊ መረጋጋት እውን ለማድረግ ትልቁን ድርሻ የሚይዙትን፤ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ተቋማትን በጠንካራ መሰረት ላይ የማዋቀሩና በቴክኖሎጂ የማዘመኑ ተግባር ከሁሉም በላይ ትኩረት የሚሰጠው መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

በተለይም እንደኛ ባሉ ቀጣይ እጣ ፈንታቸው በልማትና በልማት ላይ ብቻ መሰረት ላደረጉ ሀገራት፤ ለልማታቸው መሰረትና ቀጣይነት ዋነኛ አቅም የሆነውን ውጪያዊና ውስጣዊ ሰላማቸውን እውን ለማድረግ የግድ ይላቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ተቋሞቻቸውን አቅም መገንባትና አስተማማኝ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነትም ያስፈልጋቸዋል።

እኛም እንደ ሀገር "ድህነትን ታሪክ እናደርጋለን" በሚል እሳቤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተግባራዊ እያደረግነው ያለነውን ልማት በአስተማማኝ የሰላምና የጸጥታ መሰረት ላይ ለማዋቀር በመከላከያና በጸጥታ ተቋማት ላይ ሁለንተናዊ የሪፎርም ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ ጀምረናል። የለውጥ አመታት እንደ ሀገር በብዙ ፈተናዎች የታጠሩ ቢሆኑም፤ የሪፎርም ስራዎቹ ግን ተጨባጭ ውጤት እያስመዘገቡ ነው።

ለዚህም የሀገሪቱን የፌደራል የደህንነት እና የፖሊስ ተቋማትን ከተልእኮ ጀምሮ በሰለጠነ የሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ አቅማቸውን ለማሳደግ የተደረገው ጥረትና የተገኘው ውጤት፤ ለጎረቤት ሀገራት ምሳሌ ሊሆን የሚችል ደረጃ ላይ ደርሷል። እንደ ሀገርም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ያጋጠሙንን ውስብስብ ፈተናዎች በስኬት እንድንሻገር ትልቅ አቅም ሆነውናል።

በመከላከያና በጸጥታ ተቋማት ላይ የሚሰሩ የሪፎርም ስራዎቹ ቀጣይነት ባለው መልኩ ያለማቋረጥ በከፍተኛ ቁርጠኝነት የሚከናወኑ የብሔራዊ ጥቅማችን ማስፈጸሚያ ስትራቴጂክ ከመሆናቸው አንጻር፤ አሁን ላይ በዘርፉ እያስመዘገብነው ያለው ስኬት የምንዘናጋበት ሳይሆን ለበለጠ ስራ እራሳችንን የምናዘጋጅበት ተሞክሮ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ነው።

በተለይም በአሁን ወቅት በሀገሪቱ የሚገኙ በተለያየ የእዝ ሰንሰለቶች የሚንቀሳቀሱ የጸጥታ ኃይሎችን በአንድ የእዝ ሰንሰለት ውስጥ በማስገባት አንድ ጠንካራ ህብረ ብሔራዊ ኃይል የመፍጠሩ ሂደት፤ አንድም ሀገራዊ የጸጥታ ኃይሉን በሁለንተናዊ መልኩ ለማብቃት፣ ከዛም ባለፈ አንድ ሀገራዊ ተልእኮ ይዞ እንዲንቀሳቀስ ለማስቻል ካለው የማይተካ አስተዋጽኦ አንጻር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ሕገ መንግስታዊ በሆነ ስርአት ውስጥ የፀጥታ ኃይሎች ሰላምና ደህንነት ከማስከበር ባለፈ ህገመንግስታዊ ስርአቱን ራሱ ከየትኛውም አይነት አደጋና ስጋት የመከላከል ኃላፊነት አለባቸው። ይህንን ኃላፊነታቸውን የሚወጡት ከህገ መንግስቱ በሚመነጭ ስልጣንና ኃላፊነት ነው፡፡ በአንድ ወጥ የእዝ ሰንሰለት የመመራታቸው እውነታም ለተልእኳቸው ስኬት ወሳኝ አቅም የሚፈጥርላቸው ይሆናል።

በተለይም ሕገ መንግስታዊ የሆኑ የጸጥታ አካላት አቅም እየገነቡ ሲመጡና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት የሚያስችል ቁመና ሲላበሱ፤ በተለያዩ ምክንያቶች ሕጋዊ መሰረት ሳይኖራቸው የጸጥታ ኃይሉን ሲደግፉ የነበሩ አደረጃጀቶች ሕጋዊነት የሚላበሱበትን አሰራር መፍጠር ያስፈልጋል።

እነዚህን በአገር ሰላምና ሕልውና ማስጠበቅ ከፍ ያለ መስዋእትነት በመክፈል የድርሻቸውን ሲወጡ የነበሩ አደረጃጀቶችን በሕገ መንግስታዊ ስርዓትና ተልዕኮ በመግራት፤ የተሻለ ስልጠና እና የተልእኮ ዝግጁነት በመፍጠር ህጋዊ በሆኑ አደረጃጀቶች እንዲታቀፉ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህን በማድረግ አደረጃጀቶቹ ለሀገር ሰላም እና ለሕዝቦች ደህንነት ከቀደመው የተሻለ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትን ሕብረ ብሔራዊነትን የተላበሰ ወጥ ጠንካራ የጸጥታ እና የመከላከያ ኃይል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህም በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላምና ልማት ለማስፈን ወሳኝ ነው።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለትግራይ ሕዝብ ሰላም፣ ዴሞክራሲ እና ልማት

ዶክተር ጀኔኑስ

የታሪክ ድርሳናት እንደሚስረዱትም፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ3000 ዓመታት በላይ ወደ ኋላ ይመዘዛል። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የተለያዩ መንግስታዊ አስተዳደሮችና ሥርዓቶች ተፈራርቀዋል። እንደ ሀገርና ሕዝብ እነዚህ ሂደቶችን አልፈን አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ከ1966 ዓ.ም ቀድም ብለው የነበሩት በአብዛኛው በአፄው ሥርዓት ላይ ያተኮሩ፣ ንጉሳዊና እና ዘውዳዊ ሥርዓቶች ነበሩ። በዚሁ አስተዳደራዊ ስርአት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮቿንም ስታስተናግድ ቆይታለች። በዚህም ሀገሪቱ የቆየና፣ የጎለበተና ታሪክ ጠገብ የሀገረ መንግስት ታሪክ ባለቤት ነች። በእነዚህ ዘመናትም የተለያዩ ታሪካዊ ክስተቶችን አስተናግዳለች፤ አሁንም እያስተናገደችም ነው።

ከክስተቶቹ መካከልም ከሁለት ዓመት በፊት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተካሄደውን ጦርነት ለመመማሪያ ይሆን ዘንድ ማንሳት ተገቢ ነው። ይህ ጦርነት እንደ ሀገር በሕዝባችንም በሀገራችንም ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል። በጦርነቱ በትግራይ እና በሌሎች አጎራባች ክልል በሚኖሩ ዜጎች ላይ የሞት፣ የአካል ጉዳት መፈናቀልና የንብረት ውድመት ደርሷል። ክስተቱ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ውስጣዊ እና ውጫዊ ጫናዎች የበረቱበት ነበር። በዚህም በአገሪቱ ላይ በርካታ ጫናዎች ደርሰዋል። በፌደራሉ መንግስት እና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተደረሰው የሰላም ስምምነት በኋላ ግን ነገሮች በመልካም ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።

የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ አላማ በጦርነቱ የደረሱ ጥፋቶችን መዘርዘር ሳይሆን፤ የችግሩ ሰለባ የሆኑ ዜጎቻችንን እንዴት መካስና ማቋቋም ይቻላል በሚለው ላይ ያተኮረ ነው። በቅርቡ ወደ ስራ የገባው አዲሱ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ከዚህ አንጻር ምን ይጠበቅበታል የሚለውን ኃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ ለመጠቆም ነው።

በርግጥ ጊዜያዊ የሽግግር መንግስቱ ወይም አስተዳደሩ የክልሉ ሕዝብ ከሁሉም በላይ የሚፈልገውን ሰላም በሁለንተናዊ መንገድ የማስፈን ኃላፊነት እንዳለበት ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። ሰላም ማስፈን የቅድሚያ ቅድሚያ ስራው መሆን አለበት። ለዚህ ደግሞ እራሱን ለፕሪቶሪያው ስምምነት ማስገዛት፤ ለዚህ የሚሆነውን ቁርጠኝነቱን በየእለቱ ማደስ ይጠበቅበታል። ሰላም የሁሉም መሰረት ነውና።

ሰላሙን ተከትሎ ቀጣይ የሆነውን የሕዝቡን የልማት እና የተሻለ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በአግባቡ መመለስ ይጠበቅበታል። ከአጎራባች ክልሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ከማደስ ጀምሮ፤ በጦርነቱ ምክንያት በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ያሉ የክልሉ ዜጎችን ችግር መፍታትንም የሚያካትት መሆን አለበት። ይህንን ደግሞ የክልሉን ሕዝብ በሚመጥንና በሚገባው መልኩ ሊተገብር ይገባል።

ጊዜያዊ አስተዳደሩ የክልሉን ሕዝብ የሚመጥን ስራ መሠራት አለበት ሲባል ዘርፈ ብዙ እሳቤዎችና ትርጉሞችን ያዘለ ነው። በጦርነት ውስጥ የከረመ ሕዝብ ብዙ ነገር ያስፈልገዋል፤ ይጠይቃልም። በማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ስነልቦናዊ ምስቅልቅሎችን ለማረምና ለማስተካከል ከተለመደው አሰራር ውጭ የተለየ ቆራጥነትና የአመራር ብቃትና ጥበብ ይጠይቃል። የሁሉንም አቅሞች መጠቀምና የሕዝብ ሁለንተናዊ ተሳትፎም ያስፈልጋል። ለጋሽ አካላትን ማስተባበርና ወደ ስራ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ መፍጠርንም የግድ ይላል።

በምጣኔ ሀብት ረገድ ጦርነት የደቆሰውን መሰረተ ልማትና ኢኮኖሚው መልሶ እንዲያንሰራራ የተለያዩ አማራጮችን አስቦ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። ወደ ክልሉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጨምሮ የውጭ አገር አልሚዎች እንዲገቡ በስፋት መንቀሳቀስ፤ ለዚህ የሚሆን ግልጽ የሆነ አሰራር ማስቀመጥ እና እለት እለት አሰራሩን መቆጣጠር ያስፈልጋል። ከዚህ በፊት የነበሩና ለስራ የማይመቹ አሰራሮችና መመሪያዎች ከማረምና ከማሻሻል በዘለለ አዳዲስና ወቅቱን የሚዋጁ አሰራሮች መከተልና መመሪያዎችን ማውጣት አስፈላጊ ነው።

እንደሚታወቀው ትግራይ ብዙ ታሪካዊ ስፍራዎች፤ አስደማሚ መልክአ ምድራዊ አቀማመጦች፤ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶች የታደለች ክልል ናት። የ3000 ዓመት የሓ ጥንታዊ ቤተ መቅደስ፣ የ2000 ዓመት የአክሱም ጥንታዊ ሃውልቶች፣ ከ4ኛው እስከ 15ኛው ክፍለ ዘመን እንደተሰሩ የሚታወቁ በመቶዎች የሚቆጠሩ ከአለት ድንጋይ ተፈልፍለው የተሰሩ ውቅር አብያተክርስቲያናት እና ገዳማት እንዲሁም ሌሎች በርካታ ታሪካዊና አርኪኦሎጂካዊ ስፍራዎች የሚገኙበት ናት። እነዚህ ስፍራዎች በርካታ ቱሪስቶችን በመሳብ የክልሉን የኢኮኖሚ አቅም በማሳደግ ሊኖራቸው የሚችለው ሚና የት የለሌ ነው። አሁን ግን እነዚህ ሁሉ ስፍራዎች ከስም በዘለለ እንደ ቀድሞ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ጎብኚ የላቸውም።

የአክሱም መንደሮች የሚጎበኛቸው ባለመኖሩ ፆም እያደሩ ነው። በየዓመቱ በአክሱም ፅዮን ማርያም ንግስ በዓል የሚታደሙ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አክሱም ናፍቀዋል። አክሱምን ካዩ ሶስት አመታት አልፏቸዋል። ይህ ወደ ነበረበት መመለስ አለበት። ለሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትም እጅግ ወሳኝ ነው። በተመሳሳይ 3000 ዓመት የሓ ጥንታዊ ቤተ መቅደስ እና ሌሎች ታሪካዊ ሥፍራዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እነዚህን ወደ መስመራቸው ፈጥኖ በመመለስ ረገድ የክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር ሚና የላቀ ነው።

አዲሱ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ለዜጎች ሰላምና ደህንነት፣ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመሥራትና መኖር መብት፣ የሴቶችና ህፃናት መብት ለማክበርና ለማስከበር፤ ተፈናቃዮችንና የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ ለማቋቋም እንዲሁም ለኢትዮጵያ አንድነትም በፅናት ሊሠራ ይገባል። ሁሌም ማወቅ ያለብን ነገር አለ። ሰላም በእጃችን ነው። ሰላምን ለማስፈን ደግሞ ዋነኛ ተዋናይ መሆን ያለብን እኛው ነን።

የሰላም ባለቤት ሕዝብ ነው። ሕዝቡ ሰላሙን ሊጠብቅና ሊያስከብር ይገባል። በዚህ ውስጥ ደግሞ የመንግስትም ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በእርግጥ ጦርነት ትናንት ካስከፈለው ያልተገባ ዋጋ አንጻር ለትግራይ ሕዝብ በሰላም አስፈላጊነት ዙሪያ መንገር የሚያስፈልገው አይደለም።

እንደ ኢትዮጵያዊ ለእኛው ከእኛ በቀር ማንም አይቆረቆርልንም የሚል ጠንካራ አቋምና ባህል መያዝ አለብን። ለትግራይ ሕዝብ ከአማራና አፋር ሕዝብ በላይ የሚቆረቆር ይኖራል ብዬ አላስብም። ለአማራና አፋር ሕዝብም ከትግራይ ሕዝብ በላይ የሚቆረቆር አለ ብዬ አልገምትም። በሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ተመሳሳይ ነው።

ምንም እንኳን ያልተጠበቁ ክስተቶች ቢኖሩም የታሪክን ሁነትና የነበረውን መስተጋብር ግን የሚያናጥፈውና የሚቆረጥ ልል ገመድ ያለ አይመስለኝም። በእነዚህ ሕዝቦች መካከል የነበረው ሁኔታ አይጎድለም የሚል የፀና እምነት አለኝ። በጽኑ ታሪክና መሰረት ላይ የተገነባን መሰረት ወቅታዊ ክተተቶችና ያልታሰቡ አጋጣሚዎች ሙሉ ለሙሉ ሊያደበዝዙት አይችሉም።

ባለቤት ሲጮህ ነው ጎረቤት ሊረዳና ሊያግዝ የሚችለው። ስለዚህ እኛ የሚያምርብን እርስ በእርስ ስንረዳዳ ነው። ልማትና ዕድገት፣ ዲሞክራሲና ሁለንተናዊ ሉዓላዊነት ሊመጡ የሚችሉት ምን ጊዜም ከሰላም በኋላ ነው። ሰላም ከሌለ ሁሉም ነገር የለም። በመሆኑም በየትኛው ቦታ እና ሁኔታ ውስጥ ያለን ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ስለ ሰላም መስራት ይጠበቅብናል። ስለ አንድነትና መቻቻልም ጊዜ ወስደን መስበክ ይገባናል።

በተለይም ደግሞ የትግራይ ክልል አዲሱ አመራር ትግራይን የሚመጥን ሰላም፤ ዴሞክራሲ፤ ልማት ማስፈን የሕልውና ጉዳይ አድርጎ መውሰድ አለበት። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተገባ ዋጋ የከፈለው ሕዝብ ካጎነበሰበት ቀና እንዲልና ስነ ልቦናዊ ጫናው እንዲቃለል ብዙ አስቦ ብዙ መስራት ይጠይቃል።

መሬት የነኩ ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች በክልሉ መተግበር ለይደር የማይተው ጉዳይ ነው። ከአጎራባች ክልሎች ጋር ያለውን ቅራኔ ፈጥኖ በመፍታት የጥርጣሬ ፖለቲካን እስከ ወዲያኛው መሸኘት አስፈላጊ ነው። በአጠቃላይ በዚህ ወሳኝ ወቅት የትግራይን ሕዝብ የሚመጥን ሁሉን ተኮር ሥራ ማከናወን ከጊዜያዊ አስተዳደሩ ይጠበቃል፤ ይህንን ማድረግ ታሪካዊ ግዴታም ጭምር ነው። ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ደግሞ የሕዝቡና የሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ድጋፍም ሊለየው አይገባም።

# ነፃ ሃሳብ

## ከፉክክር ወደ ምክክር

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዓለምና እኛ ያልተግባባንበት ወይም ደግሞ ልዩነት የፈጠርንበት አንድ መስመር የማይሞላ፣ የገነገነ ልማድ አለ፤ የፉክክር መንፈስ - ትንሳኤን በፉክክር ውስጥ የመፈለግ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ልማድ።

የዓለም መልክ የምክክር መልክ ነው። የዓለም ስልጣኔ የውይይትና የተግባቦት ስልቶች አንደርስበትም። ከስልሳ ዓመት ወዲህ ያለችው ኢትዮጵያ ትንሳኤዋ የተሳለው በፉክክር ውስጥ ነው። የእኔ፣ የአንተ፤ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ ሌላም ሌላም በሚል ትርክት ውስጥ።

የዓለም ልምድም ሆነ ታሪክ እንደሚያሳየው ይህ ጽንሰ ሀሳብም ሆነ ንድፈ ሀሳብ አገርና ህዝብን አይጠቅምም። “ይጠቅማል” ከተባለ እንኳን ኢትዮጵያን ለሚጠሉና ክፉዋን ለሚመኙ ጠላቶች ብቻ ነው። ከጠቀመም የስልጣን ጥም ላለባቸው ፖለቲከኞች ብቻ ነው። ጉዟችን እንዴትም ይሁን በምክክር እስካልተራመድን ድረስ ትንሳኤ የለንም።

ትንሳኤ ቃሉ ብርሀን ነው። መሻገር ነው። መታደስ ነው። ብርሀንና መሻገር መታደስና መለወጥ በምክክር ውስጥ ካልሆነ በሌላ በምንም እንዳይደረሱ ሆነው የተቀመጡ ናቸው። አልደርስ ያልናቸው የእድገትና የስልጣኔ አምባዎች የራቁን ችግር ፈቺ የምክክር ልማድ ስለሌለን ነው።

በፍቅር ካልሆነ የስኬት መጨረሻዎች ሩቅ ናቸው። በውይይት ካልሆነ የድልና የእድል ወደቦች የማይደረሱ ናቸው። ከእኔና ከአንተ ከሌላውም ሰው በተወጣጣች አገር ውስጥ፣ በመቶ ሀያ ሚሊዮን ህዝብ ልማድና እምነት በቆመች አገር ፉክክር እያስከፈለ ያለውን አላስፈላጊ ዋጋ አለማስተዋል አሳዛኝ እውነታ ነው።

ስልጣኔ ከሀሳብ የሚጀምር የእቅድና የክዋኔ ውህደት ነው። ምክክር በታከለበት ሀሳብ አገር መፍጠር ካልቻልን በፉክክር ለማንም የማትሆንን አገር ነው የምንፈጥረው። ይሄ ደግሞ እንደመጣንበት ትላንትና በጦርነትና በእልኸኛነት እንድንቆም ከማድረግ ባለፈ እርባና የለውም።

ኢትዮጵያ የማንም አይደለችም። የሁላችንም የጋራ ቤት ናት። አለላና ስንደዶ፣ አክርማና ሰንበሌጥ በአንድ ላይ ሆነው ሞሰብ እንደሰሩ ሁሉ እኛም በአንድ ላይ ሆነን ነው ኢትዮጵያን የሰራንው። የእኔ፣ የአንተ ወይም ደግሞ በብሄር ተቧድነን ጉራጌና ሺናሻ ስንባባል ስር ሰዶ ያጠነከረንን የኢትዮጵያዊነት ገመድ እያላላን ነው።

ይሄን ሀሳብ የሚያጸና፣ ይሄን እውነት የሚያስረግጥ በምክክር የታገዘ “የእኛ” የሚል የጋራ እውነት ያስፈልገናል። እኛ እየተጋፋን ልናጠባት አያስፈልግም፣ ኢትዮጵያ ሰፊ ነች፣ ነበረች። እኛ እየተቧደንን ልናሳንሳት አይገባም፣ አገራችን ግዙፍ ነች፤ ነበረች። ክብራችን እዲገዝፍ፣ ልዕናችን እንዲጸና “እኔ”ነት የሌለባት፤ “እኛ”ነት የሰፈነባት አገር መገንባት ይጠበቅብናል።

ካለንበት ከድህነት የምንወጣበት፣ ከኋላቀርነት የምናመልጥበት አንድ አቋራጭ መንገድ የምክክር መንገድ ነው። ችግሮቻችን ችግር እየፈጠሩ፣ ፖለቲካችን ነውጥ እየፈጠረ የምንገነባው የጋራ አገር አይኖረንም። አድዋ እኮ ከአንድነት ባለፈ የምክክር ውጤት ነው። ብዙ የልዕልና ታሪኮቻችን እኮ የአባቶቻችን የአንድነትና የተግባቦት መንፈስ ነፍስ የዘራበት ነው።

ችግሮቻችንን ከዚያም ከዚም ለቅመን ለውይይት ክፍት በሆነ የጋራ መድረክ ላይ እናቅርባቸውና እንወያይባቸው። ከዛም ወደ ትንሳኤ በሚወስደን የጋራ አጀንዳ ላይ እንምከር። ይሄ ጤነኛውና አዋጩ፤ አሁን ላለችው ኢትዮጵያ የሚበጅ፣ ሞትና ጉስቁልናዋን የሚያስቀር የትንሳኤ መንገድ ነው።

**የአገራችን አብዛኞቹ ችግሮች ከፖለቲካው መንጭተው ወደ ህዝብ የሚፈሱ ናቸው። ኢትዮጵያ መጥፎ ፖለቲከኛ እንጂ መጥፎ ህዝብ የላትም። የህዝብ ፍቅር ዛሬም እንደ ድሮው በአንድነትና በኢትዮጵያዊነት የሚያምን ነው**

የአገራችን አብዛኞቹ ችግሮች ከፖለቲካው መንጭተው ወደ ህዝብ የሚፈሱ ናቸው። ኢትዮጵያ መጥፎ ፖለቲከኛ እንጂ መጥፎ ህዝብ የላትም። የህዝብ ፍቅር ዛሬም እንደ ድሮው በአንድነትና በኢትዮጵያዊነት የሚያምን ነው። ዛሬም እንደጥንቱ ተከባብሮና ተቻችሎ የሚኖር ነው። ችግር የሆኑብን ራስ ወዳድ እና አክራሪ ፖለቲከኞች ናቸው። ያልነቃና ያልበቃ ፖለቲካ ህዝብ ሊያነቃ አይችልም። ያልነቃና ያልበቃ ፖለቲከኛም አገር ሊለውጥ አይቻለውም።

ትንሳኤያችን ያለው ለአገር በሚበጅ የምክክር መንፈስ ውስጥ ነው። በእውቀት ነቅተን በእውነት ካልተራመድን ስለኢትዮጵያ መጻኢ እድል ዋስትና የለንም። ምን አይነት አሻራን እያሳረፍን እንደሆነ ራሳችንን እንጠይቅ። በኢትዮጵያ ላይ ኃላፊነት ያለበት መንግስት ብቻ እንደሆነ አምነን የተቀበልን የዚህ ትውልድ አሳቤዎች ብዙ ነን። የራሳችን ኃላፊነት የዘነጋን።

አባቶቻችን ካስተማሩን ጋር የሚጣረስ ፖለቲከኞቻችን ያስተማሩን ብዙ ልማዶች አሉን። አገር የማይገነባ፣ ወደ ነገ የማያራምድ ብዙ የስህተት ትርክቶችን ከፖለቲከኞቻችን ወስደናል። ዛሬ ላይ ያ ልማድ ነው ተነጋግረን እንዳንግባባ፣ ተመካክረን እንዳንስማማ እክል የፈጠረብን።

አባቶቻችን ያስተማሩን ስለ መቻቻል አብሮ ስለመኖር ነው። ይህም ለአገር ህልውና ወሳኝ እንደሆነ ጭምር። በእነሱ ልብ ውስጥ አገር እንጂ ብሄር የገነነ አልነበረም። ፖለቲከኞቻችን ያን የአባቶቻችንን እውነት ቀይረው የችግር ምንጭ አደረጉብን።

በአድዋ ድል ውስጥ ጥልቅ አገር ነበር። አባቶቻችን ለአንድ አገራቸው ሲሉ ነበር የተዋደቁት። እኛም ዛሬ ችግራችንን ለመፍታት፣ ከድህነት ለመውጣት የፖለቲከኞቻችን የራስ ወዳድነት እውቀት ሳይሆን የአባቶቻችን የመቻቻል እና አብሮ የመኖር እውቀት ያስፈልገናል።

አክራሪ ብሄረተኝነትትርፍ የለውም። የመከፋፈል እና ከዚህ የሚመነጭ ጥፋት ምንጭ ነው። እንደአባቶቻችን ያለ ብልህነት ውስጥ አገርን ያስቀደመ፣ ሰውነትን የተረዳ ፖለቲካዊ እውቀት ያስፈልገናል። በእውቀትና በተግባቦት የደፈረሰውን እያጠራን በአንድነት ከመኖር ውጪ አገር መገንቢያ የተሻለ እድል የለንም።

ያለፉ ስህተቶችን እየመዘዙ ለዛሬ ስልጣን መወጣጫነት መጠቀም በፖለቲካችን ውስጥ እያጋጠመን ያለው እና ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ያለ አሁነኛ ችግር ነው። ትላንትን ለትላንት ትቶ ዛሬ ላይ በአዲስ አስተሳሰብ ለመራመድ ወደ ራሳችን መመልከት ይኖርብናል።

ሁላችንም ነገ በሚመጣው ፖለቲከኛና ፖለቲካ ውስጥ ስማችን እንደሚነሳ ብናውቅ በሌሎች ስህተት ማትረፍን እንተው ነበር። ይሄንና የመሳሰለውን የፖለቲካ ልማዳችንን እስካልቀየርን ድረስ ከፉክክር አንወጣም። ከፉክክር ብቻ አይደለም ተነጋግረንም መግባባት አይቻለንም።

ምክክር የለውጥ መንገድ ነው። ተመካክረንና ተግባብተን የጋራ ችግሮቻችንን በጋራ እስካልፈታን ድረስ ለህልሞቻችን ሩቅ ነን። ፖለቲከኞቻችን ለራሳቸው የምትመችን ሳይሆን ለትውልዱ የምትመችን አገር የመፍጠር ግዴታ አለባቸው። ህዝብ የፖለቲከኞቻችንን ድምጽ ብቻ ሳይሆን አንድነት ያለበትን የአባቶቹንም አደራ ጭምር ማስታወስ ይገባል።

ካልተመካከርን የትላንት ችግሮቻችን እንዲያሰቃዩን እየፈቀድንላቸው ነው። ካልተመካከርን ለክርክርና ለፉክክር መንገድ እየጠረግን ነው። ቤት በምሰሶ እንደሚቆም ሁሉ አገርም በምክክር የምትቆም ናት። ጣሪያ፣ ማገሩ፣ ወራጅና ምርጉ በምሰሶ መኖር ህልውና የሚያገኙ ናቸው።

እንደዚህም ሁሉ አገር የብዙ ብሄርብሄረሰቦች መናኸሪያ ናት። እነዚህ ሁሉ ብዙ አይነት ማንነቶች ተከባብረውና ተቻችለው እንዲኖሩ ቤቱን እንዳቆመው ምሰሶ ምክክር ያስፈልጋቸዋል። ምሰሶ የሌለው ቤት ቤት እንደማይሆን ሁሉ ምክክርና ውይይት የሌለበት አገርም ዋስትና የለውም።

እንደአገር ብዙ የምግባባቸውም ድንገትም የማንግባባቸውም ጉዳዮች ሊኖሩን ይቻላል። ይህ ነገም ሊቀጥል የሚችል እውነታ ነው። ጥልቁ ጉዳይ በጉዳዮቹ ዙሪያ በግልጽ መነጋገር መቻል ይህንንም ባህል አድርጎ ማስቀጠል ነው። ይህ ለዛሬም ሆነ ለነገ ችግሮቻችን ትክክለኛው ፈውስ ነው።

ፈውስ በሌለውና ህመም ብቻ በሆነባት አገር ላይ የሚመጣ የትንሳኤ ብርሀን የለም። ትንሳኤ በፍቅር የሚበራ ነው። ትንሳኤ በአንድነትና በወንድማማችነት የሚቀጣጠል የተስፋ እሳት ነው። ከትናንት ያልተማሩ ህዝቦች ጠንካራ አገር አይገነቡም። የእኔነትና የራስ ወዳድነት ድምጾች በራሳቸው አገር አይቀይሩም።

“የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል” እንደሚ ባለው አገራችን በእኔና በእናንተ ፉክክር ዛሬም አልተዘጋችም። ዛሬም ክፍቷን ናት። በፖለቲካው ውስጥ ፉክክር አለ። በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ ፉክክር አለ። በአንድ አገር፣ በአንድ ታሪክ፣ በአንድ ስጋና ደም ውስጥ ቆመን ፉክክራችን ለምን እንደሆነ በቂ ተጠየቅ የለውም።

አገራችን ፉክክር አያስፈልጋትም። ተፎካክረን መጥተን ያልዘጋናቸው እልፍ የመከራ ዶሴዎች አሉን። የሚበጀን እነዛን በፉክክር ያልተዘጉ የጥላቻና የመለያየት አጀንዳዎች በምክክር መዘጋት ነው። የሚበጅን እነዛን እንዴትና በማን እንደተፈበረኩ የማናውቃቸውን መሰረት አልባ የጥላቻ ሴራዎች ማፍረስ ነው።

በእኛ ስህተት እኛ ነን የምንጎዳው። ከእኛ ውጪ ማንም የሚጎዳልን የለም። በእኔና በአንተ ፍቅር ኢትዮጵያ ክፍቱን የቀረ በራፏ መዘጋት አለበት። በእኔና በአንተ አንድነትና ወንድማማችነት እርቃ የወጣውን ገላዋ መሸፈን አለበት።

ለሁሉ የምትበቃን ሰፊ አገር የእኔ፣ የአንተ በሚል የህልውና ስጋት ውስጥ ልንከታት አይገባም። በእርቅና በምክክር ካልሆነ በፉክክርና የእኔ ያንተ በሚል መንፈስ ውስጥ ቆመን አገራችንን የጋራ ማድረግ አንችልም። የፉክክር ቤት ሁልጊዜም ክፍት ነው። ሁልጊዜም ኦና ነው። ማንም ገብቶ የሚወጣበት ባለቤት አልባ ነው።

ስንፎካከር አገራችንን ባለቤት አልባ እያደረግናት ነው። ስንፎካከር አገራችንን ለማንም እንዳትሆን እያደረግናት ነው። ከፉክክር ወጥተን መመካከር አለብን። አገራችንን የምንታደጋት አሁን ካለችበት ችግር የመንንታደጋት የእኔ፣ የአንተ ከሚል የፉክክር መንፈስ ወጥተን በጋራ ስንቆም ብቻ ነው።

እስካሁን የሄድንበት መንገድ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ አልጠቀመንም። ያን መንገድ መድገም ሌላ ዋጋ መክፈል ከመሆን ባለፈ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። ለውጥ ያስፈልገና..የባህሪ ለውጥ፣ የአስተሳሰብ ለውጥ፣ ለውጥ . . . ያስፈልገናል።

በብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን በኩል በተፈጠሩ የውይይት መድረኮች ላይ እድሎቻችንን መጠቀም አለብን። ተነጋግረን ለመግባባት፣ ተግባብተን አብረን ለመቆም ከመቼውም ጊዜ በላይ የምንተጋበት ወቅት አሁን ነው። ትላንት ዛሬን እንዳያበላሽብን፣ ዛሬ ወደ ነገ እንዳይሄድ፣ አላስፈላጊ አጀንዳዎቻችንን በምክክር እዚሁ ማስቀረት ይኖርብናል።

ማህበራዊ

## ሀገርኛ

# የመረዳዳት እና መደጋገፍ ልምምድ እንዲዳበር

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ማግኘትና ማጣት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው:: ሁለቱም ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም በሰው ልጆች የሕይወት እንቅስቃሴ ይፈራረቃሉ:: ያገኘ ሊያጣ፤ ያጣ ደግሞ ሊያገኝ የሚችልበት በርካታ አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ:: ማግኘት የመኖርን ተስፋ ሲያለመልም፤ ማጣት ደግሞ በተቃራኒው ነው ሕይወትን አጨልሞ ፈታኝና ከባድ የኑሮ ሸክምን ያሸክማል:: ያም ቢሆን ታዲያ የሰው ልጆች ማግኘትና ማጣትን አቻችለው እርስ በርሳቸው በመረዳዳትና በመደጋገፍ ስሜት ኑሮን ማጣጣም ይችላሉ:: ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው::

የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነው መረዳዳትና መተጋገዝ ከጥንት ጀምሮ በሰው ልጆች መካከል ሲከወን ቆይቷል:: ያለው የሌለውን በመርዳትና በመደጋገፍ እጅ ለእጅ ተያይዘው በአብሮነት ኑሮን መግፋት የተለመደ ተግባር ነው:: ይህ የኢትዮጵያውያን ብቻ የሚመስለው የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባህል ለሌሎች አርአያ ሊሆን የሚችል በጎ እሴት ነው::

የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባህል በሰዎች ዘንድ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም አበው ‹‹መስጠት ለራስ ነው፤ መልሶ ይከፍላል›› በማለት በሰዎች መካከል መረዳዳትና መደጋገፍ አስፈላጊ መሆናቸው ሲያስተምሩን ኖረዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉም ባለው አቅም እርስ በእርስ እየተሳሰበ፣ እየተደጋገፈና እየተረዳዳ የመኖር ባሕል ማዳበር የቻለውም ባህልና እሴቱን መነሻ በማድረግ ነው::

በዛሬው የሀገረኛ አምዳችንም በመረዳዳት ውስጥ ያሉ በጎ ተግባሮችን ለማንሳት ወደናል:: መስጠትም ሆነ መቀበል በሰጪውም ሆነ በተቀባዩ ላይ የሚፈጥረውን ስሜትም እናነሳለን::

አስናቀች አለሙ እጅ ካጠራቸውና ደጋፊ የሚፈልጉ በርካቶች መካከል አንዷ ናቸው:: እኚህ ሰው፤ ለመስጠት ባይታደሉም አጋዥ በጎ አድራጊዎች አላጡም:: ዙሪያቸው ጨለማ ሆኖ አይዞሽ ባይ ደጋፊ ባጡ ጊዜ ባዩሽ ኮልፌ በጎ አድራጎት ማህበር አባላት አይዞት አለነዎት በማለት እጃቸውን ዘርግተው እንደተቀበሏቸው ይናገራሉ::

የባዩሽ ኮልፌ በጎ አድራጎት ማህበር አባላት ከእግዚአብሔር ጋር አጋሮቻችን ናቸው የሚሉት ወይዘሮ አስናቀች፤ በየወሩ አስቤዛ እና በበዓላት ደግሞ ለበዓል የሚያስፈልገውን ሁሉ በማቅረብ የሚደፏቸው መሆኑን ናገራሉ:: ‹‹እኔ የሞትኩት ድሮ ነበር፤ ለዚህ መብቃቴ ለመናገር ቃላት ያጥሩኛል›› የሚሉት ወይዘሮ አስናቀች፤ ካለአባት የሚያሳድጉት አካል ጉዳተኛ ልጅ ያላቸው ሲሆን እንደልባቸው ተንቀሳቅሰው ሰርተው ለልጃቸው መትረፍ አቅቷቸው በችግር ላይ ወድቀው እንደነበር ይናገራሉ::

እነዚህ በጎ አድራጎት ማህበር አባላት የሰፈሩ ልጆች በመሆናቸው እሳቸውን በቅርበት የሚያውቁ ቢኖርም እቤት ድረስ በመምጣት ያሉበት ሁኔታ ተመልክተው ልባቸው ተነክቶ ድጋፍ እንዳደረጉላቸው ይገልጻሉ:: እስከዛሬ ድረስ ከሽሮ፣ በርበሬ እስከ ሽንኩርት ድረስ ሁሉም ሳይቀር በየወሩ አስቤዛ በመስጠት ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ይናገራሉ ‹‹ሥራ መሥራት አልችልም ምክንያቱም ልጄን ትምህርት ቤት የማጓጉዘው፤ አጠገቡ ሆኜ የምንከባከበው እኔው ነኝ፤ ስለዚህ ወር ሲደርስ እነሱን ነው የምጠብቀው›› የሚሉት ወይዘሮዋ፤ እርዳታ መቀበል ከጀመሩ ረጅም ጊዜ እንደሆናቸው ነው ያጫወቱን::

‹‹እኔ ሲሰጠኝ የሚሰማኝ ደስታና ሰላም ነው፤ በጣም ደስ ይለኛል›› የሚሉት ወይዘሮ አስናቀች ፤ ቤተሰብ ሆነውኝ፤ ለልጄ የአባትና የወንድምነት ፍቅር እየሰጡ፤ በዓል በመጣ ቁጥር ሥጋ ሳይቀር ሁሉም አስፈላጊ ነገር በማድረግ ይደግፉናል ይላሉ:: የወር አስቤዛቸውን አንድ ጊዜ ሳይቋረጥ በመደበኛነት እንደሚሰጣቸው ጠቁመው፤ ታዲያ ከዚህ በላይ ምን አይነት ደስታ ሊገኝ ይችላል ብለዋል ::

እዚህ እኛን የሚረዱን ልጆች ገና ተማሪ የሆኑ ወጣቶች ናቸው የሚሉት ወይዘሮዋ፤ ከእነሱ ብዙ ትምህርት ማግኘታቸው ይናገራሉ:: ‹‹እኔም ለሌላው መስጠትን፤ ማካፈልን አብሮ መጠጣትና መብላትን፤ የበረደውን ማልበስ የልቤ ምኞት ነው›› ይላሉ::

> ድጋፍ የሚደረግላቸው ሰዎች ከገንዘብ ከስጦታ በላይ የሚያስደስታቸው ፍቅር እንደሆነ በመግለጽ በተቻለ መጠን ፍቅር በመስጠት የሚፈልጉትን እንኳን ማሟላት ባንችል ከጎናቸው እንደሆንን ሲያውቁ ደስታ ይሰማቸዋልና ይህንን ማድረግ ያስፈልጋል

ወይዘሮ አስናቀች፤ እነዚህ ልጆች እኛን እንደረዱት ሁሉም ሰው ቢረዳዳ ጥሩ ነው:: መረዳዳት ያለው ለሌላው ካገኘው ላይ ማካፈል ከጥንት ጀምሮ ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ኢትዮጵያዊ ባህላችን ነውና ሁሉም ሰው ሊያደርገው የሚገባ በጎ ምግባር ነው ሲሉ ይገልጻሉ::

‹‹እኔ አሁን ቢኖረኝ ካለኝ ላይ ለሌላው ባካፍል፤ እነሱ ከሚሰጡኝ ነገር ላይ ባካፍል ደስ ይለኛል›› የሚሉት ወይዘሮ አስናቀች፤ እኔ እየበላሁ ሌላው ሲርበው፤ እኔ ለብሼ ሌላው ሲበርደው መመልከት እረፍት የሚነሳ ነው:: ሁሉም ያለው ቢያካፈል፤ ቢተባበር እጁን ቢዘረጋ፣ መልካም ተግባር ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ እጁ ሰፊ ነው፤ ደግ ነው፤ ሩህሩህ ለተቸገሩት አዛኝ፣ የወደቁትን የሚያነሳ ነውና ይህንኑ ትብብር አጠናክሮ በማስቀጠል በሚችለው አቅም ሁሉ ለተቸገሩት መድረስ አስፈላጊ ነው ብለዋል::

የባዩሽ ኮልፌ በጎ አድራጎት ማህበር መስራች ወጣት ሄኖክ ፍቃድ በበኩሉ ማህበሩ አሥር የሰፈር ጓደኛሞች ሻይ ቡና ከሚሰጣቸው ገንዘብ ላይ ቀንሰው በማሰበሳብ በዙሪያቸው ለሚገኙ አቅም የሌላቸው ተማሪ ጓደኞቻቸው ለመረዳት ብለው የጀመሩት እንደሆነ ይናገራል:: ከዛሬ 12 ዓመት በፊት ያሰባሰቡትን ብር በአንድ ላይ በማድረግ በአካባቢ ላሉ ታናናሽ ወንድምና እህቶቻቸው ደብተርና እስክብሪቶ የመሳሰሉትን የመማሪያ ቁሳቁሶችን ገዝተው በመስጠት በጎ ምግባራቸውን ‹‹ሀ›› ብለው እንደጀመሩም ያስታወሳል::

ቀስ በቀስ እያሳደጉ የመጡትን በጎ ሥራም በአካባቢያቸው የሚገኙና ብቻቸውን የሚኖሩ እናቶችን ማገዝ ቀጠሉ:: ልጆች የሌላቸው እናቶችን ልብስ እና ገላ በማጠብ፣ ምግብ በማብሰልና የመሳሰሉ በተማሪ አቅም የሚሰሩ ገንዘብ የማይጠይቁ ነገሮች በመስራት ማገዝ መጀመራቸውን የሚናገረው ሄኖክ፤ የእነሱን በጎ ተግባር ያዩ ተማሪዎችም በጎ ሥራቸውን እየተቀላቀሉ መምጣት እንደቻሉ ይናገራል::

ይህ በበጎ ፍቃደኝነት የተመሰረተ ማህበር አሁን ላይ 500 አባላት ያሉት ሲሆን የሚሰጣቸው የድጋፍ ሥራዎች ከፍ እያደረገ መምጣቱን አንስቶ፤ በዚያው ልክ የሚያግዟቸው ቤተሰቦቻቸው እየጨመሩ መምጣታቸውን ይገልጻል::

አሁን ላይ በቋሚነት የወር አስቤዛ እና የህክምና ድጋፍ የሚያደርጉላቸው ከ80 በላይ የሚሆኑ ቤተሰቦች እንዳሉ የሚናገረው ሄኖክ፤ ወርሃዊ አስቤዛ ከመስጠት ባሻገር በበዓላት ወቅት ደግሞ የሚያስፈልጉት ነገሮች በማሟላት አብረዋቸው እንደሚያሳልፉም ያወጋል:: በተጨማሪም 300 ለሚሆኑ ተማሪዎች በቻሉት አቅም የመማሪያ ቁሳቁሶችን በማሟላት፣ ቤተሰቦቻቸውን በመርዳት ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ጠቁሟል::

ሄኖክ ሰው ለመርዳት ምክንያት ስለሆናቸው ጉዳይ ሲናገር አብዛኞቻቸው ጓደኛሞች ተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ሲሆን ከእነሱ ባስ ባለ ሁኔታ የሚኖሩትን ደብተር እንኳን ሳይኖራቸው ለመማር የሚፈልጉ ሕጻናት ሲመለከቱ ማኪያቶ እና ሻይ መጠጣት ቢቀርብን እና ብናግዛቸው በሚል ሀሳብ እንደተነሳሱ ይናገራል:: ከጨዋታ በዘለለ ቁምነገር ይዘው የበጎ አድራጎት ሥራ መጀመራቸው፤ ‹‹እግዚአብሔር ይመስገን ለካ ሰውን መርዳት የሚፈጥረው ደስታ ማኪያቶ፣ ሻይ በመጠጣት ከምናገኘው ደስታ በላይ ሆነና በዚያው እንድንቀጥል አድርጎናል›› ይላል::

‹‹ሰውን መርዳት የሚሰጠውን ደስታ በቃላት የሚገለጽ አይደለም ፤ በራሴ በሕይወቴ ትህትናን ተምሬበታለሁ፣ ምስጋናን ተምሬበታለሁ፤ ያለሁበት ከማማረር ይልቅ ለምንም ነገር እግዚአብሔር ባደረገልኝ ነገር ሁሉ እንዳመሰግን አድርጎኛል›› የሚለው ሄኖክ፤ ሰውን ማገዝ ያ ሰው ያጣውን ነገር ሙሉ ለሙሉ መሸፈን እንኳን ባይችል የሆነ ነገር መካፈል መቻሉ በራሱ የሚሰጠው የተለየ ስሜት አለ ይላል:: አሁን ከሚሰጠው ደስታ ባሻገርም ነገ በሰማይ ቤት የተሻለ ነገር አለ ብለን እንድናስብ ስለሚያድርግ ትልቅ ዋጋ ያለው መሆኑን እንድናስብ ያደርገናል ብሏል::

‹‹ደስታችን የነሱ ሳቅ ነው፤ በእነሱ ላይ የሚታይ ደስታ በቃላት የማይገለጽ የተለየ ስሜት አለው›› የሚለው ሄኖክ፤ ሰው ለመርዳት በመጀመሪያ የሚያስፈልገው ሰው መሆን እንደሆነ ሁሉ ከዚያ በላይ መልካም ሥራን መስራት የሚችል መልካም ልብ እንዲሚያስፈልግ ይገልጻል::

ከዚህ ባሻገር ያሉት ሌሎች ነገሮች ቀስ እያሉ የሚመጡ መሆናቸውን አንስቶ፤ አንድ ሰው መሬት ላይ ወድቆ ሲገኝ ምን ሆነህ ነው፤ አይዞህ ብሎ ማንሳት የሚያስችል መልካም ስነልቦና እንደሚያስፈልግ ጠቁሟል:: የሰው ልጅ የወደቀ ሰውን የማንሳት፣ የመርዳትና የመደገፍ ሥራ በመስራት ሰው በመሆን ውስጥ መንገድ የማሻገር መልካም ሥራ መኖር እንዳለበት ያመላክታል::

ብቻቸውን ቀኑንን ሙሉ የሚውሉ ሰዎች ሰው ይፈልጋሉ፤ ሰው ይራባሉ የሚለው ሄኖክ ስለዚህ እነዚህን ቤተሰቦች ‹‹ደህና ዋላችሁ አደራችሁ›› ማለት አብሮ ማሳለፍ መልካምነትን የሚጠይቅ መልካም ሥራ እንደሚያስፈልግ ይናገራል:: ትንሽ ሰዓት ወስዶ አብሮ ማሳለፍ፤ ሕመማቸው፣ ጭንቀታቸውን በመጋራት እንዲሁም ልብሳቸውን ማጠብ፣ ምግብ ማብሰል፣ ገላቸው ማጠብና የመሳሳሉ መልካም ሥራዎች መሥራት የሚጠይቀው ሰው መሆን ብቻ ነው ይላል::

ብዙ ጊዜ አብዛኞቻችን የምናሰበው ሰው ለመርዳት መልካም ሥራ ለመስራት ሀብታም መሆን ወይም ካለን ላይ መስጠት ብቻ ይመስለናል የሚለው ሄኖክ፤ ከሌለን ላይ እራሱ ማድረግ እንደሚቻል ማሰብ እንደሚገባ ይገልጻል:: በተለይ ፍቅር ላይ ትኩረት በመስጠት ብቸኝነት እንዳይሰማቸው ማድረግ፣ ልጆቻቸው እንደሆንን በማስረዳት ፕሮግራም ይዞ ቡና ወይም ሻይ በማፍላት ጊዜን አብረናቸው ማሳለፍ ተመራጭ እንዲሆን ያስረዳል::

ድጋፍ የሚደረግላቸው ሰዎች ከገንዘብ ከስጦታ በላይ የሚያስደስታቸው ፍቅር እንደሆነ በመግለጽ በተቻለ መጠን ፍቅር በመስጠት የሚፈልጉትን እንኳን ማሟላት ባንችል ከጎናቸው እንደሆንን ሲያውቁ ደስታ ይሰማቸዋልና ይህንን ማድረግ ያስፈልጋል ብሏል::

በተለይም ወጣቶች ገንዘብ ባይኖራቸው ጊዜና ጉልበት ስላላቸው በመዋደድ፣ በመከባበር አብሮ በመኖር መደጋገፍ ይቻላል የሚለው ሄኖክ፤ ከምንም በላይ ደግሞ ፍቅር ያስፈልጋል:: ሰዎችን ለማገዝ መልካም ሥራንም ለመስራት የመጀመሪያ ነገር ፍቅር ሊኖረን ይገባል:: በብሔር፣ በዘርና በሃይማኖት ሳንለያይ ሰው የሆነን ፍጡር ለማገዝ የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይገባል :: ለመልካም ሥራ ረፍዶ አይውቅም ፤ ስለዚህ መልካም ሥራ ዛሬ አሁኑ መጀመር እንችላለን ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል ::

‹‹መስጠት ከሁሉም በላይ የሚጠቅመው ራስን ነው›› የምትለው የሥነ ልቦና ባለሙያ ወይዘሮ ራሔል ገብረ መስቀል በበኩሏ፤ መስጠት ጠቀሜታው ለራስ ነው:: የሚሰጥ ሰው የሚያገኘው ደስታ ከሁሉም በላይ ነው::

መስጠት ስላለን ስለተረፈን ብቻ ሳይሆን ሰው በመሆናችን ብቻ ስንሰጥ የምናገኘው ደስታ ላቅ ያለ ነው:: ለአብነት አንድ ልብስ ገዝቼ ሌላውን አውጥቼ ብሰጥ ተመልሶ ይመጣል የሚል አመላካከት አለኝ የሚሉት ወይዘሮ ራሔል፤ መስጠት ለራሳችን ከሚሰጠን ደስታ ባሻገር ስንሰጥ ደግሞ በዚያ ሰው የምናየው ደስታ ደግሞ ተመልሶ እኛኑ ያስደስተናል ይላሉ::

እሳቸው እንደሚሉት፤ መስጠትም ሆነ መቀበል ተፈጥሯዊ ናቸው:: መስጠትም ሆነ መቀበል የሚመጣው በልምምድ ነው:: መስጠትን ከልጅነታችን ካልተማርን አንለምደውም፤ ከልጅነታችን መስጠት መማር አለብን:: ወላጆች ለልጆቻችን መስጠትን ማስተማር አለባቸው:: ስንሰጠን ያ ሰው እንዲያመስግነን አስበን ሳይሆን ለራሳችን ደስታ መሆኑ እየተማርነው ፤ እየተለማመድን ካደግን እንደባህል እንቆጥረዋለን::

ለመስጠት ሰው ከመሆን ውጭ ምንም መስፈርት የለውም የሚሉት ወይዘሮ ራሔል፤ ለመስጠት የሀብት ሆነ የሌላ ነገር መኖር ያስፈልጋል የሚል እምነት የለኝም ነው የሚሉት:: ስላለን አይደለም የምንሰጠው እኛ የሚያስፈልገንን የሌለው ሌላ ሰው እንደሚያስፈልገው ማሰብ እንጂ:: ሁለት ያለው አንዱን ቢያካፍል የሚያገኘው ደስታ ጥልቅ ከመሆኑም በላይ ለተሰጠውም አካል ስጦታው ይጠቅመዋል:: ስለዚህ ይህን መሰል አመለካከትን ማሳደግ ቢችል ጥሩ ነው:: መልካም ሥራ መስራት ይቻላል ሲሉ ይገልጻሉ::

ኢትዮጵያውያን በመረዳዳትና በመደጋገፍ እያከናወኑ ያሉት ተግባር እያደገ መጥቷል:: ድጋፉ ቤተሰብን፣ ዘመድ አዝማድንና ጎረቤትን ከመደገፍ ከፍ ወዳለ ደረጃ እየተሸጋገረ ይገኛል:: እንደ መቄዶኒያ ያሉት ድርጅቶች እያከናወኑ ያሉት ተግባርና ሕዝቡ ለእነዚህ ድርጅቶች እየሰጠ ያለው ድጋፍ፣ በበዓላት ወቅት የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት እየተደረገ ያለው ርብርብ ይህ መደጋገፉና መረዳዳቱ ከፍ ወዳለ ደረጃ እየተሸጋገረ መምጣቱን ይጠቁማሉ::

ይህ ርብርብ አሁንም መጠናከር ይኖርበታል:: በሀገራችን ካሉት ደጋፍ ፈላጊ ማህበረሰቦች አኳያ ሲታይ ይህ የኢትዮጵያውያን ባህል ይበልጥ እንዲጠናከር መስራት ያስፈልጋል:: ለእዚህ ደግሞ እየተከናወኑ ያሉ የመደጋገፍና መረዳዳት ተግባሮችን ማሳየት፣ የፍላጎቱን ሰፊነት ማስገነዝብ፣ ኢትዮጵያውያን የመረዳዳት እና መደጋገፍ ባህላቸውን ይበልጥ ማስፋት ላይ መስራት እንዳለባቸው ማስረዳት ያስፈልጋል::

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ኬኮችን የማስዋብ ጥበብ

ሰላማዊት ውቤ

ቤርሳቤት በለጠ ትባላለች። ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ውስጥ ቦሌ ሚካኤል አካባቢ ሲሆን ዘንድሮ 19 ዓመቷን ይዛለች። ሳቂታና ደስተኛ ነች። ጥሩ የንባብ ባህል ያዳበረች አንባቢ ስትሆን ቤተ መጽሐፍት ውስጥ ያጠመደ አያጣትም።

እኛም ያገኘናት አብርሆት ቤተ መጽሐፍት ውስጥ ነው። ሰውነትን የሚያጠነክሩና ቅርጹን የሚያስተካክሉ ስፖርቶችን ትወድና አዘውትራ ትሰራለች። በኮሌጅ ትምህርት ባይደገፍም በትምህርት ቤት ሰልጥኖ የወጣ ሰዓሊ ከሚስለው በላይ የስእል ችሎታ አላት።

በእርሳስ የተጀመረ የስዕል ችሎታዋን ጭቃ ከለር፤ ውሃ ቀለም እያለች በየደረጃው በማሳደግ ሙሉ በሙሉ በቀለም ወደ መሳል አሸጋግራዋለች። ገቢም በሚያስገኝላት ደረጃ አድርሳዋለች። አሁን ላይ እንደውም ለኢቢኤስ ቴሌቪዥን ፕሮግራም መክፈቻ የሚሆን ታላቅ ስዕል እየሳለች ትገኛለች።

‹‹ይሄን ማድረግ የረዳኝ ኢንተርኔት ነው። በከፍተኛ ደረጃ የኢንተርኔት ተጠቃሚ ነኝ›› የምትለው ወጣት ከዚሁ ከኢንተርኔት ባገኘችው ዕውቀት በዓለም ላይ ታዋቂ የሆነችና የኢትዮጵያን ስም የምታስጠራ የኬክ አርቲስት የመሆን ህልም አላት። ህልሟን እውን ለማድረግ እንቅስቃሴ ውስጥ ከገባች ከረምረም ብላለች። ቤርሳቤት እንደምትለው የኢንተርኔት ዕውቀትን መሰረት አድርጋ የባህር ውስጥ ጥናት ወይም ተመራማሪ የመሆንም ዕቅድ በውስጧም ሰንቃለች።

‹‹በአብዛኛው ወጣቶች በመደበኛው ትምህርት ውስጥ የሥራ ፈጣሪ እንድንሆን ሳይሆን የተቀጣሪነትን አስተሳሰብ እንድንይዝ ተደርገን ነው የሰለጠነው። አሁን በተያዘው የትምህርት አቅጣጫ በቀጣዩ ትውልድ ይሄ አካሄድ ይለወጣል የሚል ዕምነት አለኝ›› የምትለው ወጣቷ ሥራ ፈጣሪ በማያደርግ ትምህርት ሥርዓት ያለፈውም ሆነ ለማለፍ የተዘጋጀው ወጣት ለውጡ ዕውን እስኪሆን ጊዜውን በከንቱ ማሳለፍ የለበትም የሚል ዕምነት አላት። ኢንተርኔትና ሌሎች አማራጮችን ተጠቅሞ የራሱን ሥራ መፍጠር ይችላል። ትምህርት, ሙያ ወይም ተጨማሪ ችሎታዎችን ጊዜና ዕድሜ የማይገድበውንም ትምህርት እስከፈለገው ድረስ ባሻው መስከ መቀጠል ይችላልም ባይ ነች።

ቤርሳቤት የ12ኛ ክፍል ትምህርቷን አምና በ2014 ዓ.ም ነው ያጠናቀቀችው። ሆኖም ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የሚያስችላት ነጥብ ለማምጣት ጠንክራ ስትሰራ ብትቆይም ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ ማምጣት አልቻለችም። ይሄን ፍላጎቷን ወላጆቿም ቢሆኑ የሚጠብቁት ነበርና ነጥብ ባለማምጣቷ ደስተኛ አልሆኑም። ቅርም ተሰኝተውባታል።

‹‹እኔ ግን ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት አለማምጣቴን ራሴን በምፈልገው መስክ ለማብቃት እንደሚያስችል መልካም አጋጣሚ ነው የወሰድኩት›› የምትለው ወጣቷ ነጥብ አምጥታ ዩኒቨርሲቲ አለመግባቷን በሰማች ማግስት ምኞቶቿን ለማሳካት ጥረት ማድረጓን ትናገራለች። ወጣቷ ለሌሎች ወጣቶች በተለይም ባለፈው ዓመት የ12ኛ ክፍል ፈተና ውጤት ላልመጣላቸውና ይሄንኑም እንደመጨረሻ ዕድል ቆጥረው በየቤታቸው ለተቀመጡ በኢንተርኔት የሚገኝ ዕውቀትን እንዲጠቀሙና በየመክሊታቸው እንዲሰማሩ መነሳሳት ትሆናቸዋለች በሚል ተሞክሮዋን ማጋራት ወድደናል።

የ19 ዓመቷ ወጣት ቤርሳቤት በለጠ እንዳ ጫወተችን ዩኒቨርሲቲ ገብታ በአንድ ትምህርት እንድትመረቅና ሥራ እንትይዝላቸው በብርቱ ይፈልጉ የነበሩት ወላጆቿ በራሷ እንድትቆም ስለሚፈልጉ አይደግፏትም። አሁን ላይ እሷን ከፍለው ለማስተማር የሚያስችል ገንዘብም የላቸውም። ቤት ገዝቶና ሰርቶ የሚያኖር አቅም ስለሌላቸው በግለሰብ ኪራይ ቤት ነው የሚኖሩት።



ወጣት ቤርሳቤት ደምሴ

**እነዚህ ግብዓቶች አገር ውስጥ መኖራቸውንና ህልሟን ዕውን ለማድረግ እንደሚያስችሏት ተገንዝባለች። ‹‹ኬክ አርቲስት መሆን የሚፈልግ ሰው ለኬክ ስለተሰሩ የሚበሉና ሰው ላይ ጉዳት የማያስከትሉ ቀለሞች አጠቃቀም ዕውቀቱ ያለው መሆን አለበት**

እንደውም በቅርቡ ዋጋው ቀነስ ያለ ቤት ለማግኘት ቀደም ሲል ይኖሩበት ከነበረው ከቦሌ ሚካኤል ሰፈር ወደ ቡልቡላ ማርያም አካባቢ ለቅቀው ሄደዋል።

‹‹ይሄ ለእኔ በፊት ከነበርንበት ቤት የበለጠ ለትራንስፖርት ወጪ የሚዳርግ ነው። ቢሆንም በአብርሆት የምፈልጋቸውን መጽሐፎች ስለማገኝ ትራንስፖርት ባጣ እንኳን በእግሬ እመጣለሁ እንጂ አልቀርም›› የምትለው ወጣቷ ከመጽሐፍትና ከኢንተርኔት የሚገኝ ዕውቀት ያለምንም ወጪ ምን አልባትም እዚህ ግባ በማይባል ወጪ ሰዎች እራሳቸውን በራሳቸው በማስተማር በዕውቀት ሊበለጽጉባቸው የሚያስችሉ መንገዶች እንደሆኑም ታወሳለች። ከነዚህ በተገኘ ዕውቀት ለገዛ ራስ የሥራ ዕድል መፍጠርና የገቢ ምንጭ ለማግኘት የሚያስችሉ ሥራዎች ላይ መሰማራት እንደሚቻልም ታነሳለች።

እሷ ንባብን ባህሏ ያደረገችውና ኢንተርኔትን የምትጠቀመው ይሄንኑ ታሳቢ አድርጋ እንደሆነም ትናገራለች። ‹‹ወጣቶች አንባቢ እና የኢንተርኔት ተጠቃሚ መሆን ብዙ ጥቅም እንደሚያስገኝ ማወቅ አለብን›› የምትለው ቤርሳቤት ስለኢንተርኔት ጥቅምም ታብራራለች። እንደማብራሪያዋ አሁን ያለንበት ዓለም ዘመናዊ ነው። የዘመናዊነት መገለጫ ደግሞ ቴክኖሎጂ ነው። ቴክኖሎጂ ማለት ሌላ ምንም ሳይሆን ኢንተርኔት ነው። አሁን ላይ በዓለማችን ብዙ ነገሮች የሚከወኑት በኢንተርኔት ነው። ኢንተርኔት የምንፈልገውን መረጃ ማግኘት ያስችለናል።

ኢንተርኔት ገንዘብ ያስተላልፋል። የምንፈልገውን ትዕዛዝም ማስተላለፍ ያስችለናል። ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ሌላ ሩቅ ዓለም ላይ ካሉ ሰዎች ጋር ተግባቦት ማድረግም ያስችላል። የራስ ገቢ ማስገኛ ሥራ መፍጠርና ወደ ተፈለገው ሙያ መግባትና ወደ ምንፈልገው አቅጣጫ ለመሄድም የሚያስችል ነው። በመሆኑም ወጣቶች ዕውቀት፤ ገንዘብ፤ ሥራ፤ የትምህርት ዕድልና ሌሎች አማራጮችን በማያገኙበት ጊዜ እንደሚያግዛቸውና የግድ የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው መገንዘብ እንዳለባቸው ትመክራለች።

‹‹አሁን ላይ ለኔ ተስፋ የሆነኝ ኢንተርኔት ነው። ግን ኢንተርኔት በራሱ ተስፋ ሳይሆን ተስፋ የሚሆነኝን ነገር ሰጥቶኛል ለማለት ነው›› የምትለው ወጣቷ በተለይ በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባ ነጥብ ባጣችበት ወቅት የደረሰላት አሌንታዋ እንደሆነም ደጋግማ ትናገራለች። እንደምትለው 12ኛ ክፍል አጠናቃ ውጤት ሳይመጣላት ሲቀር መሥራትና መሆን የምትፈልገውን በቀጥታ ያስመረጣት ኢንተርኔት ነው።

በኢንተርኔት የተለያዩ የኬክ ዓይነቶች መኖራቸውን ተረዳች። አሰራራቸው እንዴት እንደሆነም አየች። ኬክ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችንም አወቀች። ስለዚሁ የኬክ ሥራ የመሰልጠን ፍላጎትም አደረባት። ኢንተርኔት በዚሁ ላይ ተመስርታ በምትፈልገው የኬክ ሥራ እንድትሰለጥን አስቻላትና በዛው 12ኛ ክፍል ባጠናቀቀችበት ዓመት የኬክ ሥራ ለመግባት ወረቀት ያስፈልግ ነበርና በኢንተርኔት ያገኘችውን ዕውቀት ትምህርት ቤት ገብታ በተግባር በማዳበር ዲፕሎማዋን ያዘች። የኬክ ሥራ ትምህርቱን ከተማረች በኋላ ደግሞ በቅርብ ቀናት የምትመረቅበትን የምግብ ዝግጅት ስራ ትምህርትን ቀጠለች።

ወጣቷ በኬክ ስራ በዓለም ላይ እውቅና አገሯን የምታስጠራ ‹‹ኬክ አርቲስት›› የመሆን ህልሟን ለማሳካት ከኢንተርኔት የቀሰመችውን ዕውቀት በመጠቀም ቀጥላለች። ‹‹ኬክ በሚፈለገው ደረጃ ለማምረት አንድ ኬክ ለመጋገር የሚያስችለውን ሰዓት መጠበቅ ግድ ነው›› የምትለው ወጣቷ ስፖንጅ ኬክ በሦስት ደቂቃ በመሥራት ጀምራ የተለያዩ ኬኮች መጋገር ያስችላትን ብቃት ለማግኘት ስትለማመድ መቆየቷንም ነግራናለች።

ወጣቷ እንደምትለው ኬክ ሲባል ፀጥ ብሎ ክሬም የተቀባ ይመስለናል። አብዛኞቻችንም ይሄንን ነው የምናውቀው። ሆኖም በውጪው ዓለም ሙያው እንዲህ ዓይደለም። ‹‹ኬክ አርቲስት››ማለት የተለያዩ ዕውነት የሚመስሉ ሌሎች በርካታ ኬኮችን መሥራት ማለት ነው›› ትላለች። እንደ ወጣቷ የተለያዩ እንስሳት ዓይነቶችን፤ ቦርሳን፤ ሰውን የሚመስል ግን ደግሞ ዕውነተኛ ኬክ የሆኑ ኬኮችን መሥራት ደረጃ ላይ መድረስ ነው። ለዚህ ግን ጥሩ ስዕል ሰዓሊና ቅርጻ ቅርጽ አዋቂ መሆን ያስፈልጋል።

‹‹እኔ ደግሞ ከህፃንነቴ ጀምሬ እንዲህ ዓይነት ቅርፃ ቅርጾችንና ስዕሎችን እሰራ ነበር። በሁለት ዓመት ከሚበልጠኝ ወንድሜ ጋር እየተፎካከርን እነዚህን የሚመስሉ ስዕሎችን እንሰራ እንደነበር አስታውሳለሁ›› ስትልም ይሄ ከህፃንነት ጀምሮ እያዳበረች የመጣችው ልምዷ ኬክ አርቲስት የመሆን ፍላጎቷን የበለጠ በማሳለጥ ከስኬት ለማድረስ እንደሚረዳት ታወሳለች።

ሙያው በውጭው ዓለም ተፈላጊ የሚያደርግና ዳጎስ ያለ ገቢ የሚያስገኝ ነውም ባይ ነች። ሆኖም አሁን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ በትላልቅ ኢንተርናሽናል ሆቴሎች ኬክ አርቲስቶች ቢኖሩም ጥቂት ናቸው። ብቃታቸውም ቢሆን እንደውጭው ዓለም የመጠቀነው ማለት አይቻልም። የግብዓት አቅርቦት እንደተፈለገው ባለማግኘታቸውም ሆነ አቅርቦቱ የሚጠይቀው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ የሚሰሩት ሥራ በኢንተርኔት እንዳየችው ሰርክ ከምናውቀው ኬክ የተለየ፤ ማራኪና ሳቢ፤ እንዲሁም አነጋጋሪ አይደለም። ሆኖም ወጣቷ እነዚህንም ኬክ አርቲስቶች አግኝታ ልትተዋወቃቸውና ከነሱ ልምድ ለማግኘትም ሞክራለች። ከነሱ ከኢንተርኔት ካገኘችው በተጨማሪ ‹‹ኬክ አርቲስት›› መሆን የሚፈልግ ሰው ሊገለገልባቸው የሚችሉ የተለያዩ ዓይነት የኬክ ቀለሞች እንዲሁም ለኬክ መስርያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ተጋርታለች።

እነዚህ ግብዓቶች አገር ውስጥ መኖራቸውንና ህልሟን ዕውን ለማድረግ እንደሚያስችሏት ተገንዝባለች። ‹‹ኬክ አርቲስት መሆን የሚፈልግ ሰው ለኬክ ስለተሰሩ የሚበሉና ሰው ላይ ጉዳት የማያስከትሉ ቀለሞች አጠቃቀም ዕውቀቱ ያለው መሆን አለበት። ኬክ ለመሥራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ግንዛቤ ያለው መሆን ይኖርበታል ትላለች። እንዳከለችልን ኬክ አርቲስት ለመሆን የሚፈልግ ሰው በፔይስትሪ (በኬክ ሙያ) መማርና ሰልጥኖ መመረቅ አለበት። በተጨማሪም ስዕል ጎበዝ መሆን አለበት።

እሷ ስዕል ትስላለች። ጎበዝም ናት። የሳለችው ስዕል በቤተሰቧ ዙርያ፤ እንዲሁም በጓደኞቿ የገበያ ዕድል እያገኘ መጥቶ በቅርቡ አንድ ቤተክርስቲያን ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ በመወዳደር ሦስቱ ስዕሎቿ በ11 ሺህ ብር ሊሸጡላት በቅተዋል። አሁን ደግሞ ለኢቢኤስ ቴሌቪዥን የዋናው ቻናል መክፈቻ የሚሆን ድንቅ ስዕል ለማቅረብ እየሰራች ትገኛለች። ይሄ ስዕል ሲደርስ ደግሞ ዳጎስ ያለ ገቢ ሊያስገኝላት እንደሚችል ትገምታለች።

ቤርሳቤት ከኢንተርኔት ባገኘችው ዕውቀት የባህር ውስጥ ጥናት ተመራማሪ የመሆን ዕቅድም አላት። ‹‹የባህር ውስጥ ባዮሎጂስት በባህር ውስጥ የሚኖሩትን ዝርያዎች እንዲሁም ስርጭታቸውን እና የዚህ ክስተት መንስኤ የሆነውን ይለያል። እንደዚሁም በእንስሳዎች መካከል እና በእነሱ እና በአካባቢያቸው መካከል ያለውን መስተጋብር ያጠናል›› ትላለች።

ወጣቷ እንዳወጋችን ይሄ የባህር ባዮሎጂ ጥናት በግሪኩ ጠቢብ በአርስቶትል ነው የተጀመረው። አርስቶትል በርካታ የአናሌል ዝርያ፣ ክሩሴስንስ፣ ሞለስኮች፣ ኢቺኖዶርምስ እና ዓሳዎችን፤ ዶልፊኖች እና ዌል እንስሳት አጥቢዎች መስተጋብር መገንዘብ ችሏል። ሆኖም ባህር እንደስፋቱ ጥልቅ ምስጥር ያለው በመሆኑ በእሱ ያልተዳሰሱትን በሙሉ በጥናትና ምርምሯ የመሸፈን ዕቅድ አላት። ጥናቱን ካደረኩ በኋላ በዚህ ሙያ ዩኒቨርሲቲ ገብቼ የመመረቅ ዕቅድም አለኝ›› ትላለች።

ጥናቱ ሕይወት ያላቸው የባህር ውስጥ እንስሳት ላይ የሚደረግ ሳይንሳዊ ጥናት ነው ብላናለችም። እንደምትለው ትናንሽ ነፍሳት እንደ ስፖንጅ , ኑዲንጅች ወይም ማይክሮቦች በመመርመር እና ስለ ኒዩሮሳይንስ እና መድሃኒት ለመማርም ይረዳል ስትል ለወጣቶች ያጋራችውን ተመክሮ ቋጭታለች። እኛም የወጣቷ ህልም እውን እንዲሆን በመመኘት ጽሑፋችንን አበቃን።

# የምድር በረከት

## የወርቅ ማዕድን ጥናትና ማምረት ስራ - በሲዳማ ክልል

ኃይሉ ሣህለድንግል

የሲዳማ ክልል በተፈጥሮ ሀብት የታደለ ነው። ለውጪና ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርበው የቡና ሀብቱ፣ የቱሪስት መስህብ የሆነው የሀዋሳ ሀይቅና ፍል ውሃዎቹ ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳሉ:: የሲዳማ ብሔረሰብ ቱባ ባህልም ሌላው ተጠቃሽ እምቅ ሀብቱ ነው::

ክልሉ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ባሉት መሰረተ ልማቶችም ይታወቃል፤ በሀገሪቱ ሞዴል የኢንዱስትሪ ፓርክ በመባል የሚታወቀው ግዙፉ የሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የይርጋ አለም አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክና የሌሎች በርካታ ኢንዱስትሪዎችም መገኛ ነው::

ሌሎች እምቅ አቅሞቹን በማጥናት ወደ ልማት ለማስገባት ክልሉ በትኩረት እየሰራ ይገኛል:: ክልሉ ያለበትን የመሬት ጥበት ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንደ መስኖና ማዕድን ባሉት ላይም ልማቱን አጠናክሮ ለመቀጠል እየሰራ ነው::

የማዕድን ዘርፍን ብንመለከት በክልሉ በማዕድን ዘርፍ የአለኝታ ጥናቶችን በማካሄድ የማዕድን እምቅ አቅምን ለመለየትና ለማልማት የሚያስችሉ ተግባሮች እየተከናወኑ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ መስፍን መጨካ ይገልጻሉ::

በክልሉ በማዕድን ሀብቶቹ ላይ በተደረጉ ጥናቶች የወርቅ፣ የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን ማዕድናት እንደሚገኙ መለየት መቻሉን ጠቅሰው፣ የክምችቱን መጠን ለማወቅም ተጨማሪ ጥናቶች እየተካሄዱ ናቸው ይላሉ:: አንዳንዶቹን ማዕድናት የማልማት ስራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውንም ጠቁመዋል::

ዋና ዳይሬክተሩ በተለያዩ የማዕድን አለኝታ ጥናትና ልማት ስራዎች ላይ እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ያጋሩን ሲሆን፣ በዚህ ጽሁፍ በተለይ በወርቅ ማዕድን ጥናት፣ ልማትና ግብይት በኩል እየተከናወኑ ያሉ ስራዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ይዘን ቀርበናል::

### የማዕድን አለኝታ ጥናትና ልየታ

እሳቸው እንደሚሉት፤ በክልሉ በማዕድን ዘርፍ በዋናነት በትኩረት እየተሰራ ያለው በማዕድን አለኝታ ጥናት ላይ ነው:: ጥናቱም ከተለያዩ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል::

ሲዳማ በክልልነት ከተደራጀ ወዲህ ባሉት ሁለት አመታት ከጂኦሎጂካል ሰርቬይ/ የፌዴራል ተቋም ነው/ ጋር በመሆን በተለይ በወርቅ ማዕድን ላይ ጥናት አድርገናል:: በ2015 ዓ.ም የቅድመ ጥናት የቦታ ልየታ ስራ ለማከናወን ጥናት የሚካሄድበትን የቅድመ ጥናት ቦታ ልየታ ስራ አብረን ሰርተናል:: በወርቅ ላይ ከጂኦሎጂካል ሰርቬ,ይ ጋር የሚደረገው ይህ ጥናት ይቀጥላል::

ሌላው ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር እየተከናወነ ያለው ስራ ነው:: የዩኒቨርሲቲው የጂኦሎጂካል ትምህርት ክፍል ከኛ ጋር ካለፈው አመት ጀምሮ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመን በተለይ በኢንዱስትሪ ማዕድናት ላይ ጥናት ማካሄድ ተጀምሯል። ስምምነቱን የተፈራረምነው በየአመቱ ጥናት ለማድረግ ነው።በቀጣይም በጂምስቶን / የጌጣጌጥ ማዕድናት/ እና በኢንዱስትሪ ግብዓት ማዕድኖች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በኮንስትራክሽን ማዕድናት ላይም ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል ሰፊ እድል አለ::

ትልቁ የመጀመሪያ ስራችን ያለን የማዕድን ሀብት በጥናት ሙሉ ለሙሉ ያልተለየ በመሆኑ እንደ ክልል ሙሉ ትኩረት ሰጥተን እየሰራን እንገኛለን:: ስለዚህ የመጀመሪያ ስራችን ያለንን ሀብት በጥናት መለየት ነው። ትልቅ ትኩረት ሰጥተን እየሰራን ያለነው በጥናት ላይ መሆኑም ለዚህ ነው::

### በጥናት የተለዩ ማዕድናት

የተጠኑ ቦታዎችን ለወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ እየተጠቀምንባቸው ነው፤ ከወጣቶቹ አቅም በላይ የሚሆኑትን ደግሞ ጎን ለጎን ባለሀብቶች እንዲይዙት እናደርጋለን፤ በኛ ደረጃ ያሉትን በኛ ደረጃ፣ ከኛ ደረጃ በላይ የሆኑትን እንደ ጂምስቶን ያሉትን የጌጣጌጥ ማዕድናትን የፌዴራል መንግስት ፈቃድ እየሰጠን በውክልና እናስተዳድራለን፤ እያመቻቸን፣ እያቀናጀን በጋራ እንሰራለን ሲሉ አቶ መስፍን ያብራራሉ::


አቶ መስፍን መጨካ

ባለሀብቶችም ጥናት አድርገው የሚሰሩበት ሁኔታም እንዳለም ነው ዋና ዳይሬክተሩ የጠቀሱት። በጽንሰ ወርቅ ጥናት ላይ ሁለት ኩባንያዎች እየሰሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ:: እሳቸው እንደሚሉት፤ እነዚህ ኩባንያዎች ጽንሰ ወርቁን እያጠኑ ያሉት በፌዴራል መንግስት ፈቃድ መሰረት ነው:: ኩባንያዎቹ እኛ ቦታ እያስረከብን እየደገፍናቸው ጥናታቸውን እያካሄዱ ይገኛሉ:: እኛ ለወጣቶች የምንሰጠው የደለል ወርቅ ነው::

### የአነስተኛ የወርቅ ማዕድን ልማት

ወጣቶቹ እየሰሩ ያሉት በአነስተኛ የወርቅ ልማት ላይ ነው:: በዚህም ላይ በርካታ ወጣቶች ተደራጅተው እየሰሩ ናቸው:: የወጣቶቹን አቅም ለማጎልበት ሲባልም ወጣቶቹ ከባለሀብቶች ጋር ተቀናጅተው በልዩ አነስተኛ ደረጃ እንዲሰሩ እየተደረገ ያለበት ሁኔታም አለ::

በወጣቶች ደረጃ የምንሰጠው ፈቃድ ባህላዊ ፈቃድ ነው:: በባህላዊ ፈቃዱም ከአቅም በላይ የሚሆነውን በማሽን እንዲያጥቡ ኤክስካቫተር መጠቀም እንዲችሉ ወደ ልዩ አነስተኛ ወርቅ አምራችነት እናሳድጋቸዋለን፤ ወጣቶቹን ከባለሀብቱ ጋር ሰባ በሰላሳ በሚል አቀናጅተን እንዲሰሩ እናደርጋለን::

ወርቅን በተመለከተ በሲዳማ ክልል በስፋት እየሰራን ያለነው በደለል ወርቅ ላይ ነው፤ የደለል ወርቅ መጠኑ አነስ ይላል፤ የጽንሰ ወርቁ እስከሚገኝ ድረስ የደለል ወርቁን እንሰራለን:: የሚመረተው ወርቅም ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ ይደረጋል::

### ወርቅ የሚመረትባቸው የክልሉ አካባቢዎች

ወርቅ በክልሉ የገናሌን ወንዝ ይዞ በበንሳ ወረዳ ጫፍ፣ ጨቤ ጋምቤልቱ ወረዳ፣ አኮ ወረዳና በተወሰነ ደረጃ አሮሬሳ በሚባለው ወረዳ ላይ ይገኛል:: በአብዛኛው በጥናት ላይ ነው ያለው፤ ማምረቱ ላይ ገና ብዙም አልተገባበትም:: በዚህ አመት ከጂኦሎጂካል ሰርቬር ጋር በመሆን በአብዛኛው በአሮሬሳ ወረዳ ላይ ጥናት እያደረግን እንገኛለን። በወርቅ ላይ የተለየውና እና እየተሰራበት ያለው በጨፌ ጋምቤልቱ ወረዳና አብኮ ወረዳዎች ነው::

ወርቅ እየተመረተባቸውና እየተጠኑ ያሉት አካባቢዎች ከኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን ጋር ኩታ ገጠም ናቸው:: አካባቢዎቹ የሚገኙት የገናሌን ወንዝ ተከትለው ነው:: ከወንዙ ማዶ ጉጂ ነው፤ በወዲህ በኩል የሲዳማ ክልል የተጠቀሱት ወረዳዎች አሉ። ከወንዙ ማዶም ወዲህም በወርቅ ላይ እየተሰራ ነው።

በርካታ ማህበራት ወደ ስራው ገብተዋል። በተለይ በጨቤ ወረዳ ላይ ከ10 በላይ ማህበራት ይሰራሉ:: በአኮ ወረዳ ላይም ወደ ስድስት ማህበራት እየሰሩ ናቸው:: አንዳንዶች ፈቃድ ወስደው ባለሀብት እያፈላለጉ ያሉበት ሁኔታም አለ። ከመሬቱ አቀማመጥ አኳያ ከብዶናል ብለው ወደ ስራ ያልገቡም አሉ:: እነዚህ ገና ባለሀብት እያፈላለጉ ናቸው::

### የአቅም ግንባታ ድጋፍ / የወርቅ ማቅለጫና ማጠቢያ ማሽን

የተለያዩ የድጋፍ ፓኬጆችን ቀርጸን እየሰራን እንገኛለን:: ለባለሙያዎች ድጋፍ እናደርጋለን፤ ባለሙያ እንዲደግፋቸው እንዲሁም ከተሻለ ማህበር ተሞክሮ እንዲያገኙ ይደረጋል፤ በማምረቻ ቁሳቁስም ይደገፋሉ:: ለምሳሌ በዚህ አመት የወርቅ ማቅለጫ ልንገዛላቸው በጀት ይዘናል:: ለተወሰኑ ማህበራት ማሽኑን ገዝተን በሁለቱም ወረዳ አስቀምጠን የወርቅ ማቅለጫ አገልግሎት በነጻ ለማቅረብ እየሰራን ነው።

የወርቅ ማቅለጫው ፋይዳው ብዙ ነው። ማቅለጡ አንድ ነገር ነው፤ ወርቅ ወደ ሌላ አካባቢ እንዳይወሰድም አስተዋጽኦ ያበረክታል:: የተመረተውን ወርቅ በቀጥታ ወደ ባንክ ለማስገባት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

የወርቅ ማቅለጫው አምራቾቹ የወርቅ ምርታ ቸውን ለመሸጥ ወርቅ ቤቶችን ሲፈልጉ ጊዜያቸውን እና ገንዘባቸውን እንዳያባክኑ በአቅራቢያቸው ማቅለጥ እንዲችሉ ጠቀሜታ አለው። እርስ በርስ ለመተማመንም የማሽኑ ሚና ከፍተኛ ነው::

በቅርቡ የወርቅ ማቅለጫ ገዝተን ለማቅረብ አቅደናል፤ ፋይናንስ ጨረታ ለማውጣት በሂደት ላይ ይገኛል:: ማቅለጫው ከመጣ በኋላ እንዴት እንደሚጠቀሙበት ስልጠና እንሰጣለን:: ቀደም ሲልም በማህበራት አደረጃጀት ዙሪያ፣ በተለይ ከባለሀብቶች ጋር እንዴት ተቀናጅተው መስራት እንዳለባቸው እንዲሁም የእነሱ ሚና ምን መሆን እንዳለበት፣ ባለሀብቱ ምን መስራት እንደሚገባው የሚያስገነዝብ ስልጠና ሰጥተናል፤ በዚህ መሰረትም እየሰሩ ናቸው::

የወርቅ ማዕድን ጠቋሚ ማሽን ለመግዛትም ታቅዶ ነበር:: በተለይ በ2013 ዓ.ም የወርቅ ማሽኑን ለመግዛትም ታቅዶ ለግዥውም ጨረታ አውጥተን ተወዳዳሪ ባለመቅረቡ አልተሳካም።

የወርቅ ማጠቢያ ማሽን እኛ አላቀረብንም። ማሽኑን ማቅረብ ከሚችሉ ባለሀብቶች ጋር ግን ወጣቶቹን አቀናጅተናል:: በክልሉ ሶስት ቦታዎች ማጠቢያ ማሽን ይዘው የገቡ ባለሀብቶች አሉ:: ሌሎች ባለሀብቶችንም እያቀናጀን ማሽን እያስገቡ ናቸው::

የወርቅ ማጠቢያ ማሽን ገዝቶ ለማቅረብ ዋጋው ውድ ነው:: በመንግስት ደረጃ ለማህበራት የወርቅ ማሽን ገዝቶ ማቅረብ ይከብዳል:: በፌዴራል ደረጃም የተያዘው ስትራቴጂ እንደዚህ ከበድ ባለ አካባቢ ላይ የሚሰሩ ማህበራት ከባለሀብት ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማድረግ ላይ ነው፤ እኛም ያንን አቅጣጫን እየተከተልን ነው::

### የወርቅ ምርት

ባለፈው አመት ወደ 14 ኪሎ ግራም ለብሔራዊ ባንክ ገቢ መደረጉን የጠቀሱት አቶ መስፍን፣ እኛ ጋ የደለል ወርቅ ነው የሚመረተው፤ ስፋቱ ያንሳል፤ በዚህ በጀት አመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት አምስት ነጥብ ስድስት ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ገብቷል፤ በአምስት ወሩ አራት ነጥብ ስድስት ኪሎ ግራም ሪፖርት ስለመደረጉም አብራርተዋል።

### የወርቅ ምርት ግብይት

የተመረተው ወርቅ በብሔራዊ ባንክ ውክልና በተሰጠው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ይደረጋል:: ወርቁ ወደ ባንኩ እንዲገባ የሚደረገው በሁለት መልኩ ነው:: ማህበራቱ ለአዘዋዋሪዎች ካስገቡ በአዘዋዋሪዎቹ በኩል ወደ ባንክ እንዲገባ ይደረጋል:: ሂደቱን ወረዳዎችም እኛም እንከታተላለን፤ ከ50 ግራም በላይ ወርቅ ከሆነ ደግሞ ማንኛውም ማህበር ለአዘዋዋሪ አልሰጥም ካለ ራሱ ባንክ ማስገባት ይችላል።

በወርቅ አምራች ክልሎች አካባቢ የወርቅ ህገወጥ ግብይት ስለመኖሩ ይታወቃል:: በወርቅ ማጠቢያ በኩል ከባለሀብት ጋር አስተሳስረን እየሰራን ያለንበት ሁኔታ ህገወጥ ግብይቱን ይቀንሰዋል ብለን እናምናለን ሲሉ አቶ መስፍን ይገልጻሉ:: ምክንያቱም ሁለቱም ድርሻ ስላላቸው ይጠባበቃሉ፤ እዚያም ወርቁ እንዳይሰረቅ የመጠበቅ ሁኔታ ይኖራል:: አጣቢዎቹ የሚጠብቁበትም ሁኔታ አለ።ባለሀብቶቹ ማሽን ኤክስካቫተር ብዙ ወጪ አውጥተው ነው ያቀረቡት፤ ስለዚህ የመጠባበቅ ሁኔታ ስላለ የተሻለ ነገር አለ።

ከዚህ በተረፈ ወርቅ አካባቢ ላይ ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ ግብይት አለ አንልም የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ በእርግጥ ወረዳ ላይ ባለሙያዎች አሉ፤ እኛም ወደ አካባቢው ባለሙያ እየላክን ክትትል እናደርጋለን፤ ከዚያ ባሻገር ህሊና የማይወቅሰው፣ ሀገርን የሚገዳ ድርጊት የሚፈጽም ሰው ህገ ወጥ ግብይት አይፈጽምም ብለን አናምንም ሲሉ ያብራራሉ። ለዚያም ነው ከወረዳዎች የእያንዳንዱን ማህበር አፈጻጸም በየሳምንቱ የምንሰበስበው፤ ወረዳዎችም በየእለቱ ያለውን አፈጻጸም ይሰብስባሉ ይላሉ::

አቶ መስፍን እንደሚሉት፤ ከባለሀብቶች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራበት ሁኔታ ህገወጥ ግብይቱን ይቀንሰዋል:: ለእዚህም ነው እኛም አምራቾቹ ምንም አይነት ወጪ ሳያደርጉ የማቅለጫ ግዥም የምንፈጽመው:: ማሽኑን ጽህፈት ቤት አስቀምጠን ያለምንም ክፍያ እንዲያቀልጡ እናደርጋለን። ማቅለጫው ጽህፈት ቤት መቀመጡ ወርቁን በቀጥታ ወደ ባንክ ገቢ ለማድረግ ያለውን ሁኔታ ወረዳው የማወቅ እድሉን ሰፊ ያደርግለታል::

ህገ ወጥ ግብይቱን ለመቀነስ በትኩረት እንሰራለን፤ በተለይ አነስተኛ አምራቾች ከባለ ሀብቶች ጋር እንዲሰሩ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ ህገ ወጥነቱን ለመቀነስ እያስቻለ ይገኛል:: ይህ ተሞክሮ በፌዴራል ደረጃም መያዝ ይኖርበታል ሲሉ ይጠቁማሉ::

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ደግ ነፍስ..ደግ ሀሳብ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

‹ትቸር..! አለችው ከክፍል ወጥቶ ወደ ቢሮው ሲሄድ ከኋላው ተከትላ።

ለይኩን ወደ ኋላው ሲዞር ሳራን አጠገቡ አያት። ፊቱ መቆሟ አልገረመውም ሁሌ የሚያስገርመው ወደ እሱ ስትመጣ ብዙ አበሳን ነፍሷ ላይ ተሸክማ መሆኑ ነው። የነፍሷ አበሳ ይገርመዋል..እሱ ፊት እሷና ነፍሷ መከረኛ ናቸው..ለምን የሚለውን ጥያቄ ግን አልደረሰበትም።

‹እሺ ሳራ..ምን ልታዘዝ? ክፍል ውስጥ በምታውቀው ትህትናው አናገራት።

ከምትፈራው ነገሩ አንዱ ትህትናው ነው። በዛ ልክ ትሁትና ለተማሪዎቹ የተገባ መምህር ባይሆን ኖሮ አታፈቅረውም ወይም ደግሞ አትከተለውም ነበር። ሲበዛ መልካም መምህር ነው..ለተማሪዎቹ የሚሆን ብዙ ነገር አለው በዚህም ወደደችው።

መልሷ ሲርቅበት የሆነ ነገር እያሰበች እንደሆነ ገባው። ምን እንደሆነ ግን አያውቅም። ፊቱ ላይ ናት.. ረጅም ጸጉሯ በከሰዐት በኋላው ጎረምሳ ንፋስ እየተሰቃየ። ሊስቅና ሊያለቅስ በቃጣው መንታ ፊት።

‹ምነው ዝም አልሽ? ምን ላግዝሽ እያልኩሽ ነበር..› ደግሞ ጠየቃት

‹አ..አይ..ምንም..

‹ታዲያ ምን ሆነሽ ነው?

‹ዛሬ ያስተማርከን ብዙም አልገባኝም ጊዜ ካለህ በድጋሚ እንድታስረዳኝ ብዬ ነው...› ደስ የሚልና የሚያሳዝን የተማጽኖ ድምጽ ከአፏ ወጣ።

ለምን የእሱ ትምህርት እንደማይገባት አያውቅም። ክፍል ውስጥ ያልገባው አለ ብሎ ሲጠይቅ ገብቶናል ከሚሉት ውስጥ አንዷ ናት። እግሩ ከክፍል ሲወጣ ግን እንዲህ እንደአሁኑ ሌላ ናት። እሱም እንደ እሷ ብዙ ያልገባው ነገር ነበር..

‹ቅድም እኮ ስጠይቃችሁ እንደገባሽ ነግረሽኝ ነበር..› አላት የምትለውን ለመስማት እንደ ጉድ ቸኩሎ።

‹አዎ ብዬ ነበር!

‹ታዲያ አሁን ምን ተፈጠረ? በጥያቄ ፊቷ ላይ ተንቀዋለለ። የሆነ ልትነግረው የፈለገችው ነገር እንዳለ አይኖቿ አሳበቁባት። ጥያቄውን ረስቶ በልቡ ውበቷን ማድነቅ ጀመረ። ቆንጆ እንደሆነች ያውቃል። ቆንጆ ብቻ አይደለም የትኛውም ወንድ የሚፈልጋት አይነት ሴትም እንደሆነች ይሄንንም ያውቃል። አይኖቿ በቆመበት ያባብሉት ጀመር። ወንድ አይደል የሆነ ስሜት ተሰማው... በልቡ እየከጀላት መጣ። ግን የትኛውም ስሜት ለአገር ከገባው የአደራ ቃል አይበልጥበትም። የትኛውም ስሜት እምነቱን እንዲሸረሽርበት አይሻም። በሙያው አገር ሊለውጥ፣ ዜጋ ሊፈጥር ቃል ገብቷል። በተማሪዎቹ የሚወደድ ብቻ ሳይሆን የሚከበርም መምህር ለመሆን ለራሱ ቃል አለው። በቆመበት በተማሪው ላይ ያሳየውን ያልተገባ የስሜት የበላይነት አባረረ።

‹ደሞ....› የሆነ ነገር ልትለው ብላ ዝም አለች። ሀሳቧ ቆመ..ሀሳቧ ብቻ አይደለም ልቧም የቆመ ይመስላታል። ልቧ ብቻ አይደለም መኖር ያቆመችም ይመስላታል። ምን ልትለው ነበር?

‹ደሞ ምን? ከአፏ ላይ ተቀበላት።

ዝም አለችው..አንድ መዐት ዝምታ። በዝምታዋ ውስጥ ግን እሷና እሱ..ነፍሷና ነፍሱ ነበሩ። በዝምታዋ ውስጥ መቼም የማትረሳው ትህትናው..ጥሩነቱ ነበሩ። በዝምታዋ ውስጥ በእሱ ፊት በኩራት የሚያቆማት ድፍረት ብቻ ነው የሌለው። በዝምታዋ ውስጥ ብዙ አሰበች.. መምህሬ ነው.. እንደ ማፈቅረው ብነግረው እሺ ይለኝ ይሆን? አንድ ተማሪ የሚያስተምራትን ለዛውም ለሴቶች ሁሉ አስፈላጊ የሆነን መልካም መምህር ለፍቅር ብትጠይቅ ምንድነው ችግሩ? ልቧ በዝምታዋ ውስጥ ምንም ችግር የለውም ሲል መልስ ሰጣት። ተደፋፈረች። አይኗን ወዳለበት ወረወረች...የሆነ ነገር ብላለች መሰለኝ መልሷን እየጠበቀ በሚመስል ሁናቴ አገኘችው። ትዕግስቱ ይገርማታል..እንደ እሱ ሴት የሚያደምጥ ወንድ አይታ አታውቅም። ሴትን ልጅ የሚማርክ ብዙ ነገር አለው።

‹ምን እያሰብሽ ነው..? የሆነ ነገር ልትይኝ ነበር..።

በዝምታዋ ውስጥ ድምጹን ሰማችው። ድምጹ ያምራታል። ድምጹ የሰፈራቸውን የተንስኦ ጸሎት ያስታውሳታል። እሱ ሲናገርና አባ ተንስኦ ለጸሎት ሲሉ አንድ ነው። በዝምታ ወስጥ ነፍስ ዘራች..በድምጹ። አይኑ ላይ አይኗን ተክላ..በሰላ ሴትነት ወንድነቱን እየመረመረች፣ ነፍሱ ጥግ ደርሳ እየተመለሰች፣ ባልተመለሱ ብዙ ጥያቄዎች በዚህ ሁሉ ፊቱ ቆመች።

በህይወቱ ሴት አጠገብ ቆሞ ምን መናገር እንዳለበት ጥበብ የከዳው ያኔ ይመስለዋል። ምን ያክል እርግጠኛ እንደሆነ ሳያውቅ ጥያቄዋን ተቀብሎ ሊያስረዳት ወደ ቢሮ ጋበዛት።

በላመ ቀይ ፊት፣ የእሳት አሎሎ በሚመስሉ ብርሀናማ አይኖች ተከተለችው። የእሱን ባታውቅም እሷ ግን ዓለም ላይ ደስተኛዋን ሴት ሆና ነበር። ቢሮ ሲደርሱ የልቧ ድለቃ ይሰማት ነበር።

በዝምታ ወንበር ስቦ ተቀመጠ። በዝምታ አጠገቡ ወዳለው ወንበር አመላከታት። የዛሬውን የትምህርት ርዕስ የያዘውን መጽሀፍ ጠረጴዛው ላይ ዘረጋው...

አጠገቡ ናት..ነካታው። የሆነ እንግዳ ስሜት ከእሱ ወደ እሷ ሲሰርግ ይሰማታል።

‹የቱ ነው ያልገባሽ? ከእንግዳ አለሟ መለሳት።

‹እ...የሚያቃስት አይነት ድምጽ ከአንደበቷ ወጣ።

‹ይሄ አልገባኝም..› ጣቷን ወደ መጽሀፉ ጠቁማ እያሳየችው።

‹ይሄን እኮ ቅድም ጥሩ አድርጌ አስረድቻችሁ ነበር..

‹እኔ ግን አልገባኝም..።

እጇ ከመጽሀፉ ላይ ተንሸራቶ እጁን ነካው..በደንብ ያዘችው።

እያደረገች ያለው ነገር ስላልገባው ዝም አለ።

‹ትቸር..አንተ ውስጥ እንደ ሰለሞን አይነት ኃያል ጥበብ ይታየኛል።

‹ምን አይነት ጥበብ?

‹እንዲህ እንደ አሁኑ አይነት ጥበብ። ከአንተ ወደ እኔ..ከእኔ ወደ አንተ የሚፈስ የሆነ አይነት ጥበብ።

ዝም አላት..እንደ ዛሬ ምንም ነገር ገብቶት አያውቅም።

እጆቿን በዝግታ እያንቀሳቀሰች ዳሰሰችው... ሳያውቀው ከሰማያት ሰማያት ቀላቀለችው። እጆቿ አይታክቱም..እጆቿ ነፍስ አላቸው። ጣቶቿ መለኮታዊ ሀይል ተቀብተው አገኛቸው።

አይኗን ወደ አይኑ ሸቅብ ወረወረች..የሆነ ነገር ልትነግረው መሰለው..ነገረችው

‹አፍቅሬሀለው...በአንተ መከራዬን እያየሁ ነው› እንዲህ አለችው።

እንደዛሬ ደንግጦ አያውቅም። ማድረግ ያለበትን በደንብ ያውቃል። ትውልድ ሊቀርጽ ቃል ያለው መምህር ነው።

‹በጣም አዝናለው ሳራ..እኔ መምህርሽ ነኝ። አንቺን አስተምሬ ለአገርሽና ለቤተሰብሽ እንድትበቂ እንጂ ባልተገባ መንገድ ከአላማሽ ላሰናክልሽ መምህር አልሆንኩም። አንቺ ገና ልጅ ነሽ ወደ ፊት ብዙ ተስፋ ይጠብቅሻል..ትክክል ባልሆነ ነገር ህልምሽን ማጣት የለብሽም። ጥሩና ጎበዝ ተማሪ እንድትሆኚ ላግዝሽ ዝግጁ ነኝ።

ቀና ብላ አየችው..ከፍቅሩ በላይ መልካምነቱ ገዛት.. ፍቅሩን በመልካምነቱ ቀይራ እንዳላት መምህርና ተማሪ ሆነው ለመኖር ለራሷ ቃል ገባች።

# ዓለም አቀፍ

## አውሮፕላን እያበረረ ከገዳይ እባብ ጋር የተፋጠጠው ፓይለት ብሔራዊ ጀግና ተባለ

ደቡብ አፍሪካዊው ሩዶልፍ ኢራስመስ የተባለ አውሮፕላን አብራሪ እያበረረ ሳለ ከአደገኛ እባብ ጋር በመጋፈጡ አውሮፕላኑን ለማሳረፍ ተገደደ። በ11ሺህ ጫማ እየተጓዘ የነበረውን አውሮፕላን ለማሳረፍ የተገደደው ካፒቴን ኢራስመስ ነገሩ እንግዳ እንደሆነበት ለቢቢሲ ተናግሯል።

ከማብረሪያ ክፍል መቀመጫ ሥር አንዳች ነገር እግሩን ሲዳብሰው እየተንነጨው የነበረ የውሃ ላስቲክ መስሎት ነበር። ቀስ እያለ ስሜቱ ወደ ታፋው ሲሰማውና የሆነ የሚንቀሳቀስ ነገር እንዳለ ሲያውቅ ግን ግራ ገባው። “ምናልባት የፈሰሰ ውሃ እየነካኝ ይሆን ብዬ አሰብኩ” ይላል ካፒቴን ኢራስመስ። አንድ አፍታ ከሚያበረው አውሮፕላን ሰማይ ወደ መቀመጫው ጎንበስ ባለ ጊዜ ግን የተመለከተውን ማመን አቃተው። ግዙፍ እባብ መልሶ አፈጠጠበት።

ካፒቴኑ በዚያው ቅጽበት ሳይረበሽ አውሮፕላኑን



ፕሪቶሪያ አየር ማረፊያ ለማሳረፍ ተገዷል። ይህ የግል አውሮፕላን አራት ሰዎችን አሳፍሮ ነበር። ኬፕ በሚል ቅጽል የሚጠራው እባብ አንዴ ከነደፈ ገዳይ ሲሆን አንድ ሰው በዚህ እባብ ተነድፎ በሕይወት ሊቆይ የሚችለው ለግማሽ ሰዓት ብቻ ነው።

ካፒቴን ኢራስመስ “ራሴን ለማረጋጋት ሞከርኩ፤ ለተሳፋሪዎች ከተናገርኩ መረባበሽ ሊከሰት ይችላል የሚል ፍርሃት ሰቅዞ ያዘኝ” ብሏል በወቅቱ ስለተሰማው ስሜት ለቢቢሲ ሲያጋራ። በመጨረሻም በተረጋጋ ሁኔታ ‘ከቡራትና ከቡራን ተሳፋሪዎች፤ አንድ እባብ አብሮን ተሳፍሯል። እግሬ ሥር እየተርመሰመሰ ነው፤ ተረጋግተን አውሮፕላኑን እናሳርፈዋለን” ብሎ ተሳፋሪዎች ፍጹም ተረጋግተው እንዲቆዩ ተናገረ።

በዚህ ጊዜ በአራቱ ተሳፋሪዎች ዘንድ ድንጋጤው ወደ ፍጹም ዝምታና ጸሎት ተቀየረ። “በዚያ ቅጽበት መርፌ ብትወድቅ ራሱ ይሰማል፤ ሁሉም ጸጥ ረጭ ብሎ ነበር” ይላል ኢራስመስ። ካፒቴን ኢራስመስ ለቢቢሲ የተሰማውን ስሜት ሲያስረዳ አንድ አውሮፕላን አብራሪ ብዙ ያልተጠበቁ ነገሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ብዙ ስልጠና ይሰጠዋል። እባብን ማብረሪያ ክፍል ውስጥ ስለመጋፈጥ ግን ሰልጥነን አናውቅም ሲል ነገሩ ፍጹም ያልተጠበቀ እንደሆነ አብራርቷል።

በዚያ ሰዓት እንደምንም ተረጋግቶ አውሮፕላኑን ማሳረፍ ባይችል ኖሮ የከፋ አደጋ ሊደርስ እንደሚችል ተናግሯል። አውሮፕላኑ በመጨረሻ ዌልኮም ከተማ አርፏል። ነገሩን አስገራሚ የሚያደርገው ይህ አውሮፕላን ከመነሳቱ በፊት ሌሎች ሁለት በአውሮፕላን ጣቢያ የሚሰሩ ሰዎች አንዳች ተሳቢ ነገር ሲንቀሳቀስ አይተን ነበር፤ ነገር ግን ድንገት ተሰወረብን፤ አውሮፕላን ውስጥ መግባቱን አላወቅንም ብለዋል።

ካፒቴን ኢራስመስም አውሮፕላኑን ከመሳፈራቸው በፊት ውስጡን መፈተሻቸውንና ምንም እንዳላገኙ ተናግሯል። የደቡብ አፍሪካ የሲቪል አቪየሽን ኮሚሽነር ካፒቴን ኢራስመስ “በተመለከተው አስፈሪ ነገር ሳይረበሽ አውሮፕላኑን በሰላም በማሳረፉ ብሔራዊ ጀግና ነው” ሲሉ ያሞካሸው መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ሶማሊያ እና ኩባ ለ46 ዓመታት የተቋረጠውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን አደሱ

ለአራት አስርት ዓመታት የተቋረጠው ግንኙነት ኩባ አምባሳደሯን ወደ ሶማሊያ በመላክ ዳግም ተጀምሯል፡፡ ሶማሊያ እና ኩባ ከ46 ዓመታት በኋላ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ዳግም ጀምረዋል። በሶማሊያ የኩባ አምባሳደር ሆነው የተሾሙት ዩዋን ማኑዌል ሮድሪጌዝም የሹመት ደብዳቤያቸውን ለፕሬዝዳንት ሀሰን ሼህ ሞሃመድ አቅርበዋል።

የኬንያ አምባሳደርነትን ደርበው የሚይዙት ሮድሪጌዝ በሞቃዲሾ ቢሮ ባይኖራቸውም ለአራት አስርት ዓመታት ሻክሮ የቆየውን ግንኙነት ለማደስ እንደሚሰሩ ነው የሚጠበቀው። የሶማሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አማር ጃሜህም አዲሱ አምባሳደር የሞቃዲሾ እና ሃቫናን ግንኙነት ለማስተካከል ጉልህ ሚና እንደሚጫወቱ እምነታቸውን ገልጸዋል።

ሶማሊያ እና ኩባ በፈረንጆቹ 1972 በይፋ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ጀምረዋል። ከአምስት ዓመት በኋላ ሶማሊያ እና ኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ሲገቡ ግን ሃቫና ለኢትዮጵያ ወታደሮቿን መላኳ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ምክንያት መሆኑን መረጃዎች ያወሳሉ። የያኔው የኩባ መሪ ፊደል ካስትሮ ከሶቪየቶች ጋር በመሆን ለኢትዮጵያው መንግስቱ ሃይለማርያም ያሳዩት ድጋፍ የዚያድ ባሬን መንግስት ማስቆጣቱ ይታወሳል።



በአሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያም ሆነ ከሩሲያ ጋር መልካም ግንኙነት አለን ያሉት የቀድሞው የሶማሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አህመድ ኢሳ አዋድ፥ የ1977ቱ (የ1969) ጦርነት ዶሴ የተዘጋ ነው፤ ስለቀጣይ ትብብር ማሰብ ይገባል ማለታቸውን የሶማሊያ መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል።

ኩባ እና ሶማሊያ ግንኙነታቸውን ማደሳቸውን ተከትሎ ሃቫና ቀድማ የምታነሳው ጥያቄ በ2019 በሰሜናዊ ኬንያ በአልሸባብ ተጠልፈው በሶማሊያ ስለሚገኙ ሁለት የህክምና ባለሙያ ዜጎቿ እንደሚሆን ይጠበቃል። ኩባውያኑ ዶክተሮች የት እንደሚሰሩ ባይገለጽም በሶማሊያ በሚገኝ ሆስፒታል ውስጥ እየሰሩ መሆኑን የሶማሊያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃ ያሳያል። በህክምና ዘርፍ የካበተ ልምድ ያላት ኩባ በቀጣይ ከሶማሊያ ጋር በትብብር እንደምትሰራ መገለጹን አል ዐይን ዘግቧል።

# መሳው ሕዝብና የክልል ልዩ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የመንግስት ኮሙኒኬሽ አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ መንግሥት የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መጠበቅ የሚያስችል አንድ ጠንካራ የተማከለ ሠራዊት ለመገንባት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የየክልሉን ልዩ ኃይሎች ወደ ተለያዩ የጸጥታ መዋቅሮች እንዲገቡ የሚያስችላቸውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማካሄድ ጀምሯል።

መግለጫው እንዳመለከተው፤ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የልዩ ኃይል አባላት እንደ ምርጫቸውና እንደ ፍላጎታቸው በመከላከያ፣ በፌዴራል ፖሊስ ወይም በክልል ፖሊስ አባልነት መካተት ይችላሉ። በዚህ ሐሳብ ላይም ከልዩ ኃይል አመራሮችና አባላት ጋር ከመግባባት ላይ ተደርሷል። ቀደም ብሎም በሁሉም ክልል አመራሮች ጥናት ተደርጎበት፣ በተገኘው ውጤትም ያለምንም ልዩነት ውሳኔው ስምምነት ተደርሶበታል።

ይህ ተግባር እንዲፈፀም መላ ህዝባችንም ሲጠይቅ ቆይቷል ያለው መግለጫው፤ ይሄንን ተከትሎም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጀምሯል ብሏል።

መግለጫው እንዳተተው፤ የክልል ልዩ ኃይልን በተለያዩ የጸጥታ መዋቅሮች የማካተት ውሳኔና የተግባር እንቅስቃሴ በጥናት ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ነው። ይህ አካሄድ የኢኮኖሚ አቅማችንን በማሰባሰብ የሠራዊታችንን የሥልጠና፣ የትጥቅ እና የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ከፍተኛ ፋይዳ አለው። ይሄንን በመረዳትም በሁሉም ክልሎች ሂደቱ በመግባባትና በውይይት እየተከናወነ ይገኛል። ሆኖም በአማራ ክልል በሚገኙ የተወሰኑ የልዩ ኃይል ክፍሎች ውስጥ፤ በአንድ በኩል የመልሶ ማደራጀት ሥራውንና ዓላማውን በአግባቡ ባለመረዳት፤ በሌላ በኩል የጥፋት አጀንዳ አራጋቢዎች ሆን ብለው በሚነዙት የሐሰት ወሬ በመጠለፍ ሂደቱን የሚያውኩ ተግባራት ታይተዋል ብሏል።

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

ከሚነዙት የሐሰት አጀንዳዎች መካከል፤ የመልሶ ማደራጀቱ መርሐ ግብር በአማራ ክልል ብቻ እየተካሄደ ነው፤ ሕወሓት ትጥቅ ሳይፈታ እንዴት የክልሉ ልዩ ኃይል ትጥቅ ይፈታል የሚሉትና ሌሎችም ይገኙበታል ያለው መግለጫው፤ እነዚህ አጀንዳዎች ሂደቱን ለማደናቀፍ በሚፈልጉ ኃይሎች እየተናፈሱ ይገኛሉ ብሏል።

የክልል ልዩ ኃይል አባላትን ወደ ሌሎች የጸጥታ መዋቅሮች የማስገባት ፕሮግራም በመላ ሀገሪቱ የሚተገበር ነው። ሥራውም በሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ ጊዜ እየተካሄደ የሚገኝ ነው። ሂደቱንም መንግሥት በጥናት፣ በዕቅድ እና በጥንቃቄ እየመራው ይገኛል። ወደ ሌሎች የጸጥታ መዋቅሮች የማስገባት ተግባር በሚፈጸምበት ጊዜ፣ በክልሎች አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታን ለማረጋገጥ የሀገር መከላከያ ሠራዊት በሁሉም ቦታዎች ሥምሪት ወስዷል። በሌላ በኩል ሕወሓት በፕሪቶሪያው ስምምነት መሠረት ሙሉ በሙሉ ትጥቅ እንዲፈታ እየተደረገ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ብሏል የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመግለጫው።

በመግለጫው እንደተመለከተው፤ የሕወሓት ትጥቅ የመፍታት ሂደት በተፈረመው ስምምነት መሠረት ያለማወላወል የሚፈጸም እንጂ ከሌላ ሀገራዊ ዕቅድ ጋር የሚቀናጅም የሚጣረስም አይደለም። የሂደቱ ዋና ዓላማ የትኛውንም ልዩ ኃይል ትጥቅ ማስፈታት አይደለም። ልዩ ኃይሉ ትጥቁን ይዞ እና የተሻለ አቅም ተፈጥሮለት በምርጫው መሠረት የክልል ፖሊስን፣ የፌዴራል ፖሊስን ወይም የሀገር መከላከያ ሠራዊትን እንዲቀላቀል ማድረግ ነው። በዚህ ሂደት መካተት የማይፈልግ ማንኛውም የልዩ ኃይል አባል ካለ መብቱ ተጠብቆ ወደ መደበኛ የሲቪል ሕይወት እንዲገባ መንግሥት አስፈላጊውን የማቋቋም ሥራዎች ይሠራል። እንዲቋቋምም ድጋፍ ይደረግለታል፡፡

የክልል ልዩ ኃይሎችን እንደገና የማደራጀቱ ሥራ መንግሥት ለዘላቂ የሀገር ጥቅምና ደህንነት የወሰነው ውሳኔ በመሆኑ ኃላፊነቱንም በከፍተኛ ጥንቃቄ ይወጣዋል። ስለዚህ በተለያዩ የጥፋት አጀንዳ አራጋቢዎች ከሚሠራጩ አሳሳች መረጃዎች በመራቅ መላው ሕዝብ እንዲሁም የክልል ልዩ ኃይል አመራሮችና አባላት ለመርሐ ግብሩ ስኬት እንዲረባረቡ መንግሥት አሳስቧል፡፡

# በልማት ምክንያት ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሚያደርሱ ናቸው።

የነዋሪዎችን የጎርፍ አደጋ ተጋላጭነት እና በተበከሉ አካባቢዎች መኖር የሚያስከትልባቸውን ችግር ለመፍታት ነዋሪዎችን ከወንዝ ዳርቻ በማንሳት የተሻለ ንፁህ ቤት እየተሰጠ እንደሆነ የጠቆሙት ከንቲባ አዳነች፤ ከተማዋን ንጹህ፣ ውብና አረንጓዴ እንዲሁም ለኑሮ ምቹ እና የቱሪስት መስህብ ለማድረግ ከእንጦጦ እስከ ወዳጅነት ፓርክ 5 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራ ተጀምሯል ብለዋል።

ከዚህ በፊት እንደነዚህ አይነት ተግባራትን ስናከናውን ግልፀኝነት የጎደለው ነው በማለት የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመቅረፍ ሲባል በግልጽ እጣ የማውጣት ስነስርዓቱ ተከናውኗል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በተግባር የነዋሪዎቻችንን ችግር ደረጃ በደረጃ በመቅረፍ ሁሉም በፍትሃዊነት ተጠቃሚ የሚሆንባት ከተማ መገንባታችንን እንቀጥላለን ሲሉም ተናግረዋል።

አብዛኞቹ የዓለም ከተሞች ልማት የሚያከናውኑት የወንዝ ዳርቻዎችን ተከትሎ በመሆኑ የአዲስ አበባን ወንዝ ዳርቻዎች በማልማት ተወዳዳሪና የቱሪስት መዳረሻ ከተማ ለማድረግ እየሰራን እንገኛለን ብለዋል።

ከንቲባዋ አክለውም ከተባበርንና ከተጋገዝን ከችግሮቻችን በላይ በመሆን ከተማዋን እንደስሟ ውብ እና ታላቅ የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ እንችላለን ብለዋል።

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ጀማል ጀንበሩ እንደጠቆሙት ቤቶቹ የተሰጡት ከጉለሌ፣ አራዳና ልደታ ክፍለ ከተሞች በወንዝ ዳርቻና በልማት ምክንያት ለተነሱ 200 ነዋሪዎች ነው።

እንዲሁም 5 ነጥብ 6 ሄክታር መሬት ለልማት ለተነሱ ነዋሪዎች ተዘጋጅቶ በመረጡበት ስፍራ የመሬት ካርታቸውን የተረከቡ ሲሆን የራሳቸውን የመኖሪያ ቤት መገንባት እንዲችሉ 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ካሳ ለነዚሁ ተነሺዎች እንደተከፈለ ተናግረዋል።

የካንሰር ህመምተኛ እንደሆኑና ከዚህ በፊት ይኖሩበት የነበረው ስፍራ ለኑሮ የማይመች እንደ ነበረ ያስታወሱት የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ወይዘሮ ሀድራ አብደላ አሁን ላይ የዚህ እድል ተጠቃሚ በመሆናቸው ደስተኛ እንደሆኑና ከዚህ በኋላ ኑሮዋቸውን በተሻለ መልኩ እንደሚመሩ ተናግረዋል።

ለልማት ተነስተው የመሬት ካርታቸውን የተረከቡት አቶ በሀይሉ መኮንን በበኩላቸው፤ በወቅቱ ቦታቸውን ሲለቁ መንግስት ይህን እንደሚያደርግ አምነው እንደለቀቁ አስታውሰው፤ ከተማ አስተዳደሩ በገባው ቃል መሰረት አስፈላጊውን ሁሉ በመፈጸም ምትክ መሬትና ካሳ በመስጠቱ ምስጋና አቅርበዋል። ይህም ለሀገር ልማትና ለማህበረሰብ እድገት በመሆኑ ደስተኛ ነኝ ብለዋል።

ቤቶቹ ባለ አንድ፣ ባለ ሁለትና ባለ ሶስት መኝታ እንደሆኑና ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቹ የራሳቸው አሳንሰር የተገጠመላቸው እንደሆኑም ተገልጿል።

ለነዋሪዎች ተላልፈው የተሰጡ ቤቶች በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በ90 ቀናት ውስጥ ተገንብተው የተጠናቀቁ ሶስት ባለ አስራ አንድ ወለል ህንፃዎች ጳጉሜን 1/2014 ዓ.ም በከንቲባ አዳነች አቤቤ መመረቃቸው የሚታወስ ነው።

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የግዢ ጨረታ መለያ ቁጥር 002/2015ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር / ጤ/ጽ/ቤት ወረዳ 03 የመሪ ጤና ጣቢያ የ2015 ዓ/ም የ2ኛ ግማሽ ዓመት 2ኛ ዙር በግልፅ ጨረታ ግዥ ለመፈፀም ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት እቃዎች

- ሎት - 1 የደንብ ልብስ ፣ ሎት - 2 አላቂ የጽህፈት መሳሪያዎች ፣ ሎት - 3 የጽዳት ዕቃዎች ፣ ሎት - 4 የህትመት ስራዎች ፣ ሎት - 5 አላቂ የህክምና ዕቃዎች ፣ ሎት - 6 ልዩ ልዩ ዕቃዎች ፣ ሎት - 7 የጥገና እቃዎች፣ ሎት- 8 ቋሚ የቢሮ እቃዎች ጨምሮ መ/ቤቱ ባወጣው እስፔስፍኬሽን መሰረት ሎት- 9 ቋሚ የህክምና እቃዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል ፡፡ በዚህ መሰረት በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሕጋዊ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

1. በዘርፉ የተሰማሩበትን ሕጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር ለመክፈላቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
2. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በአቅራቢነት የተመዘገበ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
3. ህጋዊ እና የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያለው፣
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ(VAT) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
5. በማንኛውም ግልፅ ጨረታ ላይ ያልታገዱ መሆን አለበት ፡፡
6. ተጫራቾች ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ C.P.O.ብቻ ማቅረብ አለባቸው፡፡

| ሎት ቁጥር | የሎት ዝርዝር | የተጠየቀው የጨረታ ማስከበሪያ |
|---|---|---|
| ሎት 1 | የደንብ ልብስ | ብር 1,000.00 |
| ሎት 2 | አላቂ የጽህፈት መሳሪያዎች | ብር 2,000.00 |
| ሎት 3 | የጽዳት ዕቃዎች | ብር 2,000.00 |
| ሎት 4 | የህትመት ስራዎች | ብር 2,000.00 |
| ሎት 5 | አላቂ የህክምና ዕቃዎች | ብር 6,000.00 |
| ሎት6 | ልዩ ልዩ ዕቃዎች | ብር 1,000.00 |
| ሎት 7 | የጥገና ዕቃዎች እን የጥገና ስራዎች ጭማር | ብር 3,000.00 |
| ሎት 8 | በቋሚ የቢሮ እቃዎች | ብር 10,000.00 |
| ሎት 9 | ቋሚ የህክምና እቃዎች | ብር 10,000.00 |

7. የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰነድ የማይመለስ ብር 100.00/ አንድ መቶ ብር / በመክፈል የተዘጋጀውን ሰነድ ከተቋሙ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 52 እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ ፡፡
8. ተጫራቾች ጨረታው ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 10/አሥር / ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በመሪ ጤና ጣቢያ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 52 ድረስ በመምጣት ዋጋው የተሞላበትን የጨረታ ሰነዱን ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ለየብቻው በማሸግ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
9. ጨረታው በ10ኛው ቀን ከጥዋቱ 2፡30 እስከ 7፡50 ድረስ ክፍት ሆኖ በዚሁ ቀን ከሰአት በኋላ 8፡00 ላይ ታሽጎ በዚሁ እለት 8፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ የጨረታው መዝጊያና መከፈቻ የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን እና በተጠቀሰው ተመሳሳይ ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወከሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
10. ተጫራቾች ላሸነፉባቸው ጠቅላላ ዋጋ የውል ማስከበሪያ 10% ማስያዝ አለባቸው፡፡
11. ተጫራቾች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ለሚወዳደሩበት ናሙና ለሚቀርብባቸው ዕቃዎች ናሙና ማቅረብ አለባቸው ፡፡ ናሙና የማይቀርብባቸው ቋሚ ዕቃዎች መስሪያ ቤቱ ባቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ አለባቸው፤ በተጨማሪም በፎቶ /ማንዋል/ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
12. በጨረታ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠ ድርጅት ያሸነፈበትን ዕቃ በራሱ ትራንስፖርት ወረዳ 03 መሪ ጤና ጣቢያ ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
13. መ/ቤቱ ለጨረታ ከቀረበው ዕቃ እስከ 20% የመቀነስም ሆነ የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
14. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በመሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ማሳሰቢያ፡-እያንዳንዱ ዋጋ ሲሞላ ቫትን ጨምሮ ሆን አለበት፡፡ ዘግይቶ የመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡

አድራሻ፡- ለሚኩራ/ክ/ከ/ወረዳ 03 መሪ ጤና ጣቢያ አያት አደባባይ አልፎ ወደ አራብሳ በሚወስደው አስፓልት ዞን 57 መንገድ በኮሮኮንች መግቢያ መንገድ 1500 ሜትር ገባ ብሎ ይገኛል፡፡

ስልክ ቁጥር፡- **0118680705**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ /ወ/03/መ ጤ/ጣ**

# ስፖርት





## ጎረቤታሞቹን ያገናኘው የፕሪሚየር ሊጉ 18ኛ ሳምንት መርሃ ግብር ጨዋታ

አስማየሁ ግዛው

ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ከዋልያዎቹ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ መልስ ከ17ኛ ሳምንት መርሃ ግብር ከጅምሮ በአዳማ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ የ17ኛ ሳምንት ቀሪ መርሃ ግብሮችን ተስተካካይ ጨዋታ ባሳለፍነው ሳምንት ያስተናገደው ፕሪሚየር ሊጉ ዛሬ በ18ኛ ሳምንት መርሃ ግብር ጨዋታዎች ይቀጥላል፡፡

በዚህም ዛሬ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ስቴድየም ሁለት ጨዋታዎች ይካሄዳሉ፡፡ 9፡00 ሰዓት ላይ የሊጉን መሪ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከሲዳማ ቡና የሚያገናኘው ጨዋታ ተጠባቂ ነው፡፡ ፈረሰኞቹ መሪነታቸውን ለማጠናከር፤ ሲዳማ ቡናዎች ደግሞ በሊጉ ያላቸውን ቆይታ ለማረጋገጥ የሚደረግ ጨዋታ መሆኑ ተጠባቂ አድርጎታል፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከድል መልስ ሲዳማ ቡና ደግሞ ከሽንፈት መልስ የሚያደርጉት ፍልሚያም ነው፡፡ ፈረሰኞቹ በ17ኛ ሳምንት ተስተካካይ መርሃ ግብር ኢትዮ-ኤሌክትሪክ 2 ለ 0 በሆነ ውጤት በማሸነፍ መሪነታቸውን ማጠናከራቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ሲዳማ ቡና በበኩሉ በሀዲያ ሆሳዕና ከደረሰበት የ1 ለ 0 ሽንፈት ማግስት ጨዋታውን ያደርጋል፡፡

ዛሬ አርባ ምንጭ ከተማን ከመቻል የሚያገናኘው ጨዋታም የሚጠበቅ ሲሆን፣ አዞዎቹ ከዚህ ጨዋታ ነጥብ በማግኘት ከወራጅ ቀጠናው ለመውጣት፤ መቻል ደግሞ ደረጃውን ለማሻሻል የሚያደርጉት ፍልሚያ ይሆናል፡፡ አርባ ምንጭ በተስተካካይ መርሃ ግብር አዳማ ከተማን አስተናግዶ የ3ለ2 ሽንፈት ማስተናገዱ የሚታወስ ሲሆን አርባ ምንጭ በበኩሉ በኢትዮጵያ መድን የ2 ለ 1 ሽንፈት እንደደረሰበት ይታወቃል፡፡

የሳምንቱ መርሃ ግብር ጨዋታዎች ነገና ከነገ በስቲያ ቀጥለው የሚካሄዱ ይሆናል፡፡ ነገ 9፡00 ሰዓት ላይ ኢትዮጵያ ቡናን ከወልቂጤ ከተማና፣ 12፡00 ሰዓት ደግሞ ፋሲል ከነማን ከባህር ዳር ከተማ የሚገናኙ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያ ቡና እና ወልቂጤ ከተማ በውጤት ቀውስ ውስጥ ሆነው የሚያደርጉት ጨዋታ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ቡና ከሃዋሳ ከተማ ያለምንም ግብ ወልቂጤ ደግሞ በባህር ዳር ከደረሰበት አስደንጋጭ ሽንፈት በኋላ የሚያደርጉት መርሃ-ግብር ነው። በደረጃ ሰንጠረዡም ቢሆን ኢትዮጵያ ቡና ወደ መሪዎቹ ለመጠጋትና ወልቂጤ ከተማ ደግሞ ከወራጅ ቀጠናው ለመራቅ የሚደረግ ጨዋታ እንደመሆኑ ተጠባቂ ነው፡፡

የጣና ሞገዶቹ በተስተካካይ መርሃ ግብራቸው ወልቂጤ ከተማን 4ለ0 በመርታት ከጣፋጭ ድላቸው መልስ ነገ ጎረቤታቸውን ሲገጥሙ፣ አፄዎቹ በበኩላቸው ወላይታ ድቻን 2ለ1 በረቱ ማግስት በዚህ የውድድር ዓመት ጥሩ አቋም ላይ ከሚገኙት የጣና ሞገዶች ጋር ይፋለማሉ፡፡ ሁለቱም ተጋጣሚዎች ከድል ማግስት የሚደርጉት ጨዋታ በመሆኑም በጉጉት ከሚጠበቁ ጨዋታዎች አንዱ ሆኗል፡፡ ባህር ዳር ከመሪው ቅዱስ ጊዮርጊስ ያለውን ነጥብ ለማጥበብ፤ አፄዎቹ ደግሞ ወደ መሪዎቹ ለመጠጋት የሚያደርጉ ፍልሚያም እንደመሆኑ ተጠባቂ ነው፡፡

እሁድ 9፡00 ሰዓት ላይ አዳማ ከተማ ከሃዋሳ ከተማ ይገናኛሉ፡፡ አዳማ በተስተካካይ ጨዋታው መቻልን አሸንፎ፣ ሃዋሳ ደግሞ ከኢትዮጵያ ቡና ነጥብ ተጋርቶ የሚያካሄዱት ጨዋታ ነው፡፡ በደረጃ ሰንጠረዥም ሃዋሳ ከተማ አራተኛ ሲሆን መቻል ስምንተኛ ደረጃን ይዞ ይገኛል፡፡ ሁለቱም ውጤት በመያዝ በደረጃ ሰንጠረዡ ከፍ ለማለት የሚያደረጉት ጨዋታም ይሆናል። በተመሳሳይ እሁድ 12፡00 ሰዓት ላይ ኢትዮ-ኤሌክትሪክ እና ወላይታ ድቻ ከውጤት ማጣት በኋላ የሚገናኙ ክለቦች ናቸው፡፡ በ17ኛ ሳምንት ተስተካካይ መርሃ ግብር ኢትዮ-ኤሌክትሪክ በመሪው ቅድስ ጊዮርጊስ የደረሰበትን የ2ለ0 ሽንፈት ለማካካስ ወላይታ ዲቻ ደግሞ በፋሲል ከነማ ከደረሰበት ሽንፈት ለማገገም የሚያደርጉት ጨዋታ በመሆኑ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ተጠባቂ ነው፡፡ ውጤቱ በተለይም ለኢትዮ-ኤሌክትሪክ እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ ክለቡ በአሁኑ ወቅት በወራጅ ቀጠና ግርጌ ስለሚገኝ ከዚህ ጨዋታ ነጥብ ማሳካት ይኖርበታል፡፡

የ18ኛ ሳምንት መርሃ ግብር የመጨረሻ ጨዋታዎች ሰኞ ቀጥለው ሲደረጉም ሀዲያ ሆሳዕና ከድሬዳዋ ከተማ ይጫወታሉ፡፡ ሁለቱም የሚገናኙት ከሽንፈት መልስ ነው። ከዚህ ጨዋታ ነጥብ ይዞ ለመውጣትና ደረጃቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉት ፍልሚያ በመሆኑም ተጠባቂ ነው፡፡ ሰኞ 12፡00 ሰዓት ላይ በሚያስተናግደው የለገጣፎ ለገዳዲ እና ኢትዮጵያ መድን ጨዋታ የ18ኛ ሳምንት መርሃ ግብር የሚያጠናቅቅ ይሆናል፡፡ ለገጣፎ ከ15 ጨዋታዎች በኋላ አሸንፎ እና ኢትዮጵያ መድን እንዲሁ ከድል መልስ ነው የሚገናኙት፡፡ ለገጣፎ ያለበትን የውጤት ቀውስ ለመቅረፍና ከወራጅ ቀጠና ለመውጣት ኢትዮጵያ መድን ወደ መሪው ለመጠጋት የማይሆኑት እልህ አስጨራሽ ጨዋታ እንደሚሆንም ይጠበቃል፡፡

የደረጃ ሰንጠረዡን ቅድስ ጊዮርጊስ በ38 ነጥቦችና በ26 የግብ ክፍያ ይመራል፡፡ ባህርዳር ከተማ ከጊዮርጊስ በ5 ነጥቦች አንሶ 33 ነጥቦችን በመያዝ ሁለተኛ ላይ የተቀመጠ ሲሆን፣ የሊጉ ክስተት ኢትዮጵያ መድን እንዲሁ በ33 ነጥቦች በግብ ክፍያ አንሶ 3ኛ ደረጃን ይዞ ይገኛል፡፡ ኢትዮ-ኤሌክትሪክ 8፣ ለገጣፎ በ9 እና አርባምንጭ ከተማ በ18 ነጥቦች ወራጅ ቀጠና ውስጥ ይገኛሉ፡፡





## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 392 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0062835915 ኡመር ሲራጅ አሊ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ንፋስ ስልክ ላፍቶ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ደረሰኝ ከቁጥር 001 እስከ 164 የተሰራበት እና ከቁጥር 165 እስከ 250 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀስው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ንፋስ ስልክ ላፍቶ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡ ኡመር ሲራጅ አሊ**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁ 659 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (Tin) 0004832545 ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ ከተመዘገቡበት ቂርቆስ ክ/ከተማ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ካሳተመው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 78401 እስከ 78413 የተሰራበት እንዲሁም ከ78414 እስከ 78450 ድረስ ያሉት ደረሰኞች ደግሞ ያልተሰራባቸው ሲሆኑ በአንድነት ከነጥራዙ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

ነገር ግን ከደረሰኞቹ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከኩባንያው በሕጋዊ መንገድ ግዢ ያከናወነ ወይም ክፍያ ለመፈጸም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡ ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀነራል ኢንሹራንስ አ.ማ**

## ማስታወቂያ

“ኑሰይባ በጎ አድራጎት ማህበር” የተባለ ማህበር ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን መስሪያ ቤት የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ተቃዋሚ ካለ እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን መስሪያቤት ህብረት ኢንሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 406 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

## ማስታወቂያ

”ኬር ለምን እኔ እያለሁ በጎ አድራጎት ድርጅት” የተባለ አገር በቀል ድርጅት “ቦርድ መር“ ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ተቃዋሚ ካለ እስከ ሚያዝያ 05 ቀን 2015 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ህብረት ኢንሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

## ማስታወቂያ

ኖላዊ የሴቶችና ህፃናት መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት የተባለ አገር በቀል ድርጅት ከዚህ በፊት ያልነበረ ሲሆን ከዚህ በታች በተቀመጠው አርማ የሚጠቀም መሆኑን እያሳወቀን

ተቃዋሚ ካለ እስከ ሚያዝያ 05 /2015 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ሕብረት ኢንሹራንስ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ድረስ ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ ማቅረብ የሚችል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን**

## የስም ማስታወቂያ

ሐጋይ አሉሚናይ አሶሲየሽን ኢትዮጵያ (HAGGAI ALUMNI ASSOCIATION ETHIOPIA) የተባለ የሃይማኖት ተቋም ምዝገባ ለማድረግ ያመለከተ በመሆኑ በዚህ ስያሜ እና ዓርማ ተቃውሞ ያለው አካል ካለ በ10 ቀናት ውስጥ ለኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ይቅረብ፡፡

**የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል**